
ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 338 ነሐሴ 8 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለወጣቱ ምን ዕድል ይዞ ይመጣል?

**መዓዛ ማሞ**

**ዜና ትንታኔ**

በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው አዲሱ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የኢትዮጵያ መንግሥት ገልጿል፡፡ የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎም የውጭ አገር የምንዛሪ ተመን በገበያው ዋጋ እንዲተመን በመደረጉ በርካታ የውጭ ሀገር ኢንቨስተሮች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው በተለያዩ ዘርፎች ሊሰማሩ እንደሚችሉ የምጣኔ ሀብት ምሁራን ይናገራሉ፡፡

ይህ በቅርቡ ይፋ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በኢኮኖሚው ላይ ለውጦች እንደሚያመጣም እሙን ነው።፡ ማሻሻያው በተለይ ለወጣቱ ምን ዕድሎች ይዞ ይመጣ ይሆን? ኢኮኖሚው ላይስ ምን አይነት ለውጦች ያመጣል? እንዲሁም ምን ጥንቃቄዎች መደረግ አለበት? በሚሉት ጉዳዮች ላይ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች የተለያዩ ዕይታዎችን አካፍለውናል፡፡

የፐብሊክ ፖሊሲና የምጣኔ ሀብት ምሑር ቆስጠንጢኒዮስ በርኽተስፋ (ዶ/ር) የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ትልቅ ለውጥ ይዞ እየመጣ ነው ይላሉ፡፡

**የማክሮ ኢኮኖሚ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**



# ሀገራዊ ምክክር ከሌሎች የሠላም ግንባታ ሂደቶች በምን ይለያል?

**አማን ረሺድ**

**ዜና ትንታኔ**

በየዘመናቱ ሳይመለሱ ለቀሩ የሕዝብ ጥያቄዎች መፍትሔ ለማበጀትና ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር ሀገራዊ ምክክር ወሳኝ ሚና አለው። ምክክሩ በአለመግባባት የሚባክን ሀብትና የሰው ሕይወትን በመታደግ ዘላቂ ሠላምን የሚያጸና ነው፡፡

ምክክር፣ ድርድርና ሽምግልና ለዘመናት ላጋጠሙ ችግሮች መፍቻ ቁልፍ ከመሆን አልፈው እንደ ሕግም የሚከበሩና የሚተገበሩ ባሕላዊ ዕሴቶቻችን ሆነው አገልግለዋል።

ሀገራዊ ምክክር ለሀገራችን ኢትዮጵያ አዲስ ልምምድ እንደመሆኑ መጠን ፅንሰ ሀሳቡ ከሌሎች የሠላም ግንባታ ወይም ከግጭት አፈታት ሂደቶች ጋር እየተቀላቀለ ብዥታን ሲፈጥር ይስተዋላል፡፡

የምክክር፣ የድርድር እና የሽምግልና ልዩነቶች እንዲሁም አንድነቶች ምንድን ናቸው? ከሌሎች የሠላም ግንባታ ሂደቶች

**ከሌሎች የሠላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

# ከርምጃ ባሻገር

**ሳሙኤል ወንደሰን**

**ዜና ትንታኔ**

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ይፋ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በተደረገ ክትትል እና ቁጥጥር በሕገ-ወጥ ተግባር ላይ ተሠማርተው በተገኙ ሰባት ሺህ 676 ነጋዴዎች ላይ አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ መወሰዱን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገልጿል፡፡

ማሻሻያው ተግባራዊ ከተደረገበት ጀምሮ በተካሄደ የገበያ ክትትል እና ማረጋጋት ሥራ እስከ ነሐሴ 1 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ አለአግባብ ዋጋ በጨመሩ ሰባት ሺህ 312 ተቋማት ላይ የማሸግ እንዲሁም በ42 ተቋማት ላይ ፈቃድ የማገድ ርምጃ መወሰዱንም ይፋ ተደርጓል፡፡

በተመሳሳይ የ36 የንግድ ተቋማት ፈቃድ ሲሰረዝ፣ በ286 ሕገ ወጥ ነጋዴዎች ላይ ደግሞ የእስራት ቅጣት ተጥሏል፡፡ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ መመሪያ ትግበራ እና በንግድ ሥርዓቱ ላይ የሚደረገው ክትትል እና ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ከሚኒስቴሩ የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡

**ከርምጃ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**






# አርብቶ አደሩን ከሥጋት የሚታደገው መድን

ውብሸት ሰንደቁ

**ዜና ሐተታ**

አቶ ተስፋዬ ኡይገለች በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ነዋሪ ናቸው፡፡ ከክልሉ ነዋሪነትም ባሻገር በአርብቶ አደርና ቆላማ ጉዳዮች ቢሮ የአርብቶ አደር የአደጋ ሥጋት ቅነሳ እና አካታች የኢኮኖሚ ዕሴት ማሻሻያ ፕሮጀክት አስተባባሪ ሆነው ያገለግላሉ፡፡

በክልሉ በሬና ላሞችን፣ ፍየልና በጎችን የሚያረቡ በተለይ በአርብቶ አደርነት ብቻ የሚተዳደሩ እንዳሉ የሚጠቅሱት አቶ ተስፋዬ፤ በግለሰብ ደረጃ ከ800 እስከ አንድ ሺህ የቁም እንስሳት ያሏቸው አርብቶ አደሮች መኖራቸውን ይናገራሉ፡፡

ሆኖም የቁም እንስሳት ደኅንነት አጠባበቅ ላይ ተለምዷዊ እንጂ በዘመናዊነት የታገዘ አካሄድ እንዳልነበረ ጠቁመው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አርብቶ አደሮች ላይ በተፈጠረ ግንዛቤ የቁም እንስሳት መድን መግባት መጀመራቸውን ያብራራሉ፡፡

በክልሉ ስምንት የሚደርሱ የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ወረዳዎች መኖራቸውን የሚጠቅሱት አስተባባሪው፤ የአደጋ ሥጋት ቅነሳ እና አካታች የኢኮኖሚ ዕሴት ማሻሻያ ፕሮጀክት በስምንቱም ወረዳዎች እየተተገበረ እንደሚገኝ ይናገራሉ፡፡

በወረዳዎቹ የሚገኘው የአርብቶ እና ከፊል አርብቶ አደር ማኅበረሰብ ቁጥር ከ750 ሺህ በላይ እንደሆነ ጠቁመው፤ የቁም እንስሳት መድን የመግባት ባሕል ገና እየዳበረ ያለ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡

አቶ ተስፋዬ እንደገለጹት፤ ከዚህ ቀደም በክልሉ መጠነኛ ድርቅ ተከስቶ 537 አርብቶ አደሮች ላይ ሥጋት ተደቅኖ ነበር፡፡ እንደወትሮው ቢሆን ብዙ እንስሳት ሊሞቱ እና ለጉዳት ሊዳረጉ የሚችሉበት ዕድል ሰፊ ነው፡፡

አርብቶ አደሮቹ የቁም እንስሳት ኢንሹራንስ የገቡ በመሆናቸው፤ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጎ የውሃና የመኖ አቅርቦት ማግኘታቸውን ተናግረዋል፡፡ በዚህም የቁም እንስሳታቸውን ከሞት ራሳቸውን ከኪሳራ አድነዋል ይላሉ፡፡


አቶ ተስፋዬ ኡይገለች

ማኅበረሰቡ ከመድኅኑ በሚያገኛቸው የቁጠባ ጉርሻ አገልግሎቶችም የእንስሳት የውሃ አቅርቦት እና የመኖ ቅድመ ዝግጅት እያደረገ እንደሚገኝም ነው የተናገሩት፡፡

በክልሉ በአርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች ዘንድ በተፈጠረ ግንዛቤ ከ530 በላይ የአካባቢው ነዋሪዎች ለቁም እንስሳቶቻቸው መድን ( ኢንሹራንስ) መግባታቸውን ያስገነዝባሉ፡፡

ሆኖም ይህ ቁጥር በቂ እንዳልሆነ የሚጠቅሱት አስተባባሪው፤ ማኅበረሰቡን ከሥጋት እንስሳቱን ከሞት ለማዳን ሲባል የቁም እንስሳት መድን ላይ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

የክልል እና የፌዴራል መንግሥታት የቁም እንስሳት መድን ፕሮጀክቶችን ትኩረት ሰጥተው የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደሩን የሕይወት ዘይቤ ሊቀይሩ ይገባል ሲሉም ይመክራሉ፡፡

በሬዕ አብዱርሃማን መሐመድ በሱማሌ ክልል የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር የአደጋ ሥጋት ቅነሳ እና አካታች የኢኮኖሚ ዕሴት ማሻሻያ ፕሮጀክት አስተባባሪ ናቸው፡፡

በክልሉ ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ሁለት ዓመቱ መሆኑን የሚናገሩት አቶ በሬዕ፤ በተለይ የቁም እንስሳት(መድን) ኢንሹራንስ ላይ በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝ ያመላክታሉ፡፡


በሬዕ አብዱርሃማን

ማኅበረሰቡ እንደ ግመል እና ፍየል ያሉ ተፈላጊነት ያላቸው የቁም እንስሳትን የሚያረባ ቢሆንም የአካባቢው የአየር ንብረት አስተማማኝ እንዳልሆነ ይጠቅሳሉ፡፡

በመሆኑም የቁም እንስሳት መድን አስፈላጊ መሆኑን ተናግረው፤ በክልሉ የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ዘንድ ያለው የቁም እንስሳት ግንዛቤ እየጨመረ መምጣቱን ያብራራሉ፡፡

በክልሉ 85 በመቶ የሚጠጋው ነዋሪ አርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ነው የሚሉት አቶ በሬዕ፤ ሁሉም አካባቢዎች የቁም እንስሳት መድን ተጠቃሚ ለመሆን ፍላጎት ቢኖራቸውም በክልሉ ከሚገኙ 95 ወረዳዎች 24 ወረዳዎች ብቻ ፕሮጀክቱ እየተተገበረባቸው እንደሚገኝ ይናገራሉ፡፡

ፕሮጀክቱ እየሠራባቸው ከሚገኝባቸው 24 ወረዳዎች 66 ሺህ አርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች የቁም እንስሳት መድኅን መግዛታቸውንም ይናገራሉ፡፡

እንደ አስተባባሪው ገለጻ፤ በክልሉ ያሉ የቁም እንስሳት 50 ሚሊዮን ይጠጋሉ፡፡ የቁም እንስሳት (መድን) ኢንሹራንስ በመግባት በድርቅ ጊዜ የእንስሳት መኖ እና ውሃ አቅርቦት ማግኘት የግድ የሚባል ጉዳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2021 እና በ2022 ዓመታት ብቻ ከአምስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ እንስሳትን በድርቅ ምክንያት አጥታለች የሚሉት ደግሞ የአደጋ ቅነሳ እና አካታች የኢኮኖሚ ዕሴት ፕሮጀክት ብሔራዊ አስተባባሪ አቶ ጀማል አልይ ናቸው፡፡


አቶ ጀማል አልይ

መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ የእንስሳት መድን (ኢንሹራንስ) እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አስረድተው፤ አሁንም በመላ ሀገሪቱ ለ140 ሺህ አርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደሮች ተደራሽ የቁም እንስሳት መድን መሸጡን ይናገራሉ፡፡

የቁም እንስሳት መድን ዘርፉን ከስጋት ነፃ ለማድረግ እና ለማዘመን የሚረዳ መሆኑን ጠቁመው፤ የቁም እንስሳት መድኅን አርብቶ አደሩን ከስጋት እንስሳቱን ከሞት የሚታደግ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ከኦሮሚያ፣ ሶማሌ፣ አፋር እና ደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች በተውጣጡ 187 ወረዳዎች ተግባራዊ የሚደረግ ነው።

ፕሮግራሙ የሚተገበረው በደቡብ ኢትዮጵያ ደቡብ ኦሞ ስድስት ወረዳዎች፤ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ፣ ቀብሪ ደሐር እና ጅርቲ በሚገኙ 95 ወረዳዎች፤ በኦሮሚያ ያቤሎ፣ ባሌ ሮቤ እና ጭሮ በሚገኙ 45 ወረዳዎች ነው። በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ምዕራብ ኦሞ እና ከፋ በሚገኙ ስምንት ወረዳዎች እንዲሁም በአፋር አዋሽ ሰባት በሚገኙ 35 ወረዳዎች ይተገበራል።

# በክልሉ 285 ሚሊዮን ችግኞችን በአንድ ጀንበር ለመትከል ዝግጅቶች ተጠናቀዋል

## - ከ5 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ይሳተፉበታል ተብሎ ይጠበቃል

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል 285 ሚሊዮን ችግኞችን በአንድ ጀንበር ለመትከል የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መጠናቀቃቸውን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዳይሬክተር አቶ እስመለዓለም ምሕረት ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በዘንድሮ ዓመት ለሚከናወነው የአንድ ጀንበር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር በአማራ ክልል ከ285 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በ28 ሺህ 500 ሄክታር መሬት ላይ በአንድ ጀንበር ለመትከል የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቅቀው እለቱ እየተጠበቀ ነው፡፡

በዚህ የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር በክልሉ የሚገኙ 22ቱም ዞኖች ተሳትፎ ያደርጋሉ ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከላይኛው ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ባለው መዋቅር መልዕክት መተላለፉንና ከ5 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ተሳትፎ ያደርጉበታል ተብሎ እንደሚጠበቅ ጠቁመዋል፡፡

በክልሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ካለፈው ዓመት ጀምሮ ሲከናወኑ መቆየታቸውን አስታውሰው፤ በዚህ ዓመትም ለየት ባለ ሁኔታ ከዚህ ቀደም የተተከሉ ችግኞችን የመንከባከብና የመተካት ሥራዎች እንደሚሠሩ ተናግረዋል፡፡



እንደ አቶ እስመለዓለም ገለጻ፤ በደጋ፣ በቆላ፣ በወይና ደጋና በሌሎችም እንደየአከባቢው የአየር ሁኔታ ተስማሚነት ያላቸው ችግኞች የሚተከሉ ይሆናል፡፡ በዚህም የግራር፣ ባሕርዛፍ፣ የወይራ፣ የሀበሻ ፅድ እንዲሁም እንደአቮካዶ፣ ማንጎና ሌሎችም ለምግብነት የሚውሉ የፍራፍሬ ችግኞች ይተከላሉ፡፡

ለተከላውም በአብዛኛው ለደን፣ ለጥምር ግብርና፣ ለውበትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ ችግኞች መዘጋጀታቸውን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ መርሐ ግብሩን የተሳካ ለማድረግ የመረጃ ቅብብሎሹን ሊያሳልጥ የሚችል ቴክኒካል ኮሚቴ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ በማዋቀር እንቅስቃሴዎች እየተከናወኑ ነው ብለዋል፡፡

አቶ እስመለዓለም፤ በ2016 ዓ.ም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በ201 ሄክታር መሬት ላይ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ችግኞች ለመትከል ታቅዶ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን በመግለጽ፤ የማስጀመሪያ ሥነ ሥርዓቱ ሰኔ 26 ከተደረገ ጊዜ ጀምሮ በክልሉ ያለው የዝናብ ስርጭት የተሻለ በመሆኑ መርሐግብሩ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል ነው ያሉት፡፡

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር በርካታ ለውጦችን እያስገኘ እንደሚገኝ የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ የተተከሉም ሆነ የሚተከሉ ችግኞች የፅድቀት መጠናቸው እንዲጨምርና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማግኘት እንዲቻል ጥረት እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ የአረንጓዴ ዐሻራ ትልቅ ሀሳብ በመሆኑ ለችግኝ ተከላው የሚወጡ ዜጎች ችግኞቹን በምን አይነት መልኩ በመንከባከብ ለፍሬ ማብቃት እንደሚቻል መወያየት አለባቸው። እንዲሁም ግንቦት ሲመጣ ችግኝ መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ዜጋ ከችግኝ የማፍላት ሂደት ጀምሮ ተሳትፎ ማድረግ አለበት፡፡

# - የፓስፖርት ዋጋ ማሻሻያው ተገቢ አለመሆኑን የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ገለጹ
# - የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ከወጪው አንጻር ማሻሻያው ተመጣጣኝ ነው ብሏል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት የአሠራር ማስተካከያና ማሻሻያ ሳያደርግ በዋጋ ላይ ያደረገው ጭማሪ ተገቢና ፍትሐዊ ያልሆነ፣ የመንግሥትንም ክልከላ የጣሰ ነው ሲሉ ተገልጋዮች ቅሬታ አቀረቡ፡፡ የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎቱ በበኩሉ ማሻሻያው ከወጪው አንጻር ፍትሐዊና ተመጣጣኝ ነው ብሏል፡፡


ስማቸውን መግለጽ ያልፈለጉ ቅሬታ አቅራቢዎች አሠራሩ አሁንም መሻሻል የሚጠበቅበት፣ ብዙ ችግሮችም ያሉበት ሆኖ ሳለ የዋጋ ጭማሪ መቅደሙ ተገቢ አይደለም ብለዋል፡፡

መታረም ያለባቸው በርካታ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ይስተዋላሉ፣ ተቋሙ የአሠራር ማስተካከያ ሳያደርግ የዋጋ ማሻሻያ ብቻ ነው ያደረገው ሲሉ ወቀሳ አቅርበዋል፡፡

ጭማሪው በጣም ይከብዳል፣ የማይታሰብና የማይገመት ነው ያሉት ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ ቅሬታ አቅራቢዎች፤ በመደበኛ ሲከፈል በነበረው ላይ በአንዴ ሦስት ሺህ ብር ተጨምሮበት እንዲከፈል መደረጉ ተገቢ አይደለም፣ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍልንም ያገናዘበ አይደለም ሲሉ ቅሬታቸውን ገልጸዋል፡፡

መንግሥት ማንኛውም ጭማሪ እንዳይደረግ በከለከለበት ማግስት ተቋሙ ያደረገው ጭማሪ ተቀባይነት የሌለው፣ የመንግሥትን ውሳኔ እና ክልከላ በግልጽ የሚጥስ መሆኑንም ቅሬታ አቅራቢዎቹ ተናግረዋል፡፡

የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት የሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ ዳይሬክተር አቶ ሙሉጌታ ታደሰ፤ አገልግሎቱ ለረጅም ጊዜ ትችት የበዛበት፣ ሕዝብ የሚያለቅስበት፣ ብዙ ቅሬታ ስሞታና እንግልት የሚቀርብበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡ አሠራሩን ለማሻሻል ቴክኖሎጂውን በመቀየር፣ በሰው ኃይል፣ በማቴሪያልና በአጠቃላይ አደረጃጀት ማሻሻያ የማድረግ ተግባር አንድ




ዓመት ወስዷል ነው የሚሉት፡፡

ፓስፖርቱ የውጭ ምንዛሪ የሚያስወጣ በመሆኑ በነበረው ክፍያ ብንቀጥል የምናወጣውና የምናስከፍለው ዋጋ ተመጣጣኝ አይሆንም፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ ለዚህ አገልግሎት የመንግሥት ድጎማ ሊያስፈልገን ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሁሉም ነገር መቶ በመቶ ሥርዓት ጠብቋል፣ ተስተካክሏል እያልን አይደለም፣ ነገር ግን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመንቀስ እያስተካከልን እንገኛለን፣ ተቋሙ ከሚያደርጋቸው ትግበራዎች የዋጋ ታሪፍ ማሻሻያ የሪፎርሙ አንድ አካል ነው፡፡ ይህ ባይሆን ደግሞ ችግሩ በነበረበት ሊቀጥል ይችላል ሲሉ አቶ ሙሉጌታ ስጋታቸውን ተናግረዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ አምስት ዓመት የሚያገለግል፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚቀርበው የተከበረ ሰነድ ተመጣጣኝ ክፍያ ነው የተተመነው፡፡

በመደበኛ ክፍያ አምስት ሺህ ብር እንዲከፈል የተወሰነው ከምናወጣው ወጪ አንጻር ፍትሐዊና ተመጣጣኝ ዋጋ ነው ብለን ነው የምናምነው ያሉት ኃላፊው፤ በየእያንዳንዱ ነገር ላይ መንግሥት ድጎማ ሊያደርግ አይችልም ብለዋል፡፡

ደንበኛው ለደላላና ለተለያዩ ወጪዎች ከሚዳረግ አሠራርን ማዘመን ተገቢ ነው ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ ደንበኞችን እቤት ድረስ ማገልገል ጀምረናል፣ ተግባሩንም ኅብረተሰቡ ሊያበረታታው ይገባል ብለዋል፡፡

ለበርካታ ጊዜ ሳይስተናገዱ የቆዩ ደንበኞችን እሁድን ጨምረን እያገለገልን፣ ውዝፎችንም እያጠራን እንገኛለን። በፊት እስከአምስት ቀናት ይፈጅ የነበረውን እስከ ምሽት ድረስም ቢሆን ቆይተን በማስተናገድ ጉዳያቸውን እንዲጨርሱ እያደረግን ነው፡፡

በመደበኛ አዲስ ፓስፖርት ከስድስት እስከ ሰባት ወራት፤ እድሳት ደግሞ ከ15 ቀናት እስከ አንድ ወር አካባቢ ይፈጃል፡፡ ይህንን ወደዜሮ ለማድረስ አቅደናልም ብለዋል፡፡

ትግበራው ሕገወጥ ደላሎችን ያስወጣል፣ የተገልጋዮችን ውጣ ውረድ ያስቀራል፣ በተቋሙ የሚስተዋሉ የአሠራር ችግሮችንም ይቀርፋል ሲሉም አብራርተዋል፡፡


አያይዘውም ምንም እንኳን አሁን ካለው የዋጋ ግሽበት ጋር በተያያዘ ችግሮች ቢኖሩም መቀየር አለበት። አሠራሩን አሻሽሎ፣ ሥርዓት ፈጥሮ ወደተግባር መግባቱ ግዴታ ነው፡፡ ደንቡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀ ሦስት ወራት ሆኖታል፡፡ አሁን የተጀመረ አይደለም ብለዋል፡፡

አገልግሎቱ ተመጣጣኝ እንዲሆን፣ ተደራሽ ለማድረግ፣ በርካታ ቅርንጫፎችን ለመክፈት ለማስፋፊያ ሥራም የዋጋ ታሪፍ ማሻሻያ ማድረጉ አስፈላጊ ነው ያሉት፡፡

አገልግሎቱ ባደረገው ማሻሻያ አዲስ ፓስፖርትም ሆነ የፓስፖርት እድሳት በመደበኛ ቀድሞ ሁለት ሺህ ብር ሲያስከፍል የነበረው በታሪፍ ዋጋ ማሻሻያው ወደ አምስት ሺህ ብር ማደጉ፤ አስቸኳይ በሁለት ቀናት 25 ሺህ ብር፤ በአምስት ቀናት ከሆነ ደግሞ 20 ሺህ ብር ከፍ ማለቱ እንዲሁም እድሳት እና እርማት ደግሞ መደበኛ 12 ሺህ 500 ብር፤ አስቸኳይ በሁለት ቀናት 32 ሺህ ብር እንደደረሰ ይፋ መደረጉ ይታወሳል፡፡

# በክልሉ ከቱሪስቶች ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዷል

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ከቱሪስቶች ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት መታቀዱን የክልሉ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአማራ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዓባይ መንግሥቴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ 2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስትራቴጂክ እቅድ የመጨረሻ ዓመትና ለቀጣዩ አምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ መሸጋገሪያ በመሆኑ ከቱሪዝም ማግኘት የታቀደውን ገቢ ለማሳካት ከፍተኛ የሆነ ርብርብን የሚጠይቅ ነው፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት 23 ሺህ የውጭ ሀገር ጎብኚዎች እና አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን በማስተናገድ ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት መታቀዱን አስታውቀዋል፡፡

የተያዘውን እቅድ ለማሳካት የክልሉን የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች በማልማትና በማስተዋወቅ የውጭና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ወደ ክልሉ መጥተው እንዲጎበኙ የማድረግ ሥራ እንሠራለን ብለዋል፡፡

የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ጥበቃና እንክብካቤ የማድረግ እና የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተገቢውን አገልግሎት እንዲያቀርቡ በማድረግ የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ የማራዘም ሥራ በትኩረት እንደሚሠራ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የቱሪስት መዳረሻ ባሉባቸው አካባቢዎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሆቴሎች፣ ሎጂዎችና ሪዞርቶች በአግባቡ በመገንባት ለቱሪስቶች ምቹ የማድረግ ሥራ መሠራቱን ገልጸው፤ በገበታ ለሀገር ንቅናቄም የአካባቢውን ወግና ባሕል ጠብቆ የተሠራው የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት ግንባታ ተጠናቆ ለጎብኚዎች ክፍት መደረጉን ተናግረዋል፡፡

የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት ለአካባቢው ገጽታ ግንባታ፣ ሌሎች አልሚዎችን ለመሳብ እና የቱሪስቶችን ቆይታ ለማራዘም ከፍተኛ አስተዋፅዖ የሚያበረክት መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በገበታ ለትውልድ ንቅናቄም የሎጎ ሐይቅ ኢኮ ሪዞርት ግንባታ እየተከናወነ ሲሆን፤ በቀጣይ ትልቅ የቱሪስት መዳረሻ ይሆናል ብለዋል፡፡

ለነባር የቱሪስት መዳረሻዎች ጥገና እና እንክብካቤ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራ ገልጸው፤ በ2016 በጀት ዓመት ክልሉ 74 ሚሊዮን ብር በመመደብ እና በኅብረተሰብ ተሳትፎ 32 ለሚሆኑ ልዩ ልዩ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች የጥገና ሥራ መጀመሩን አስረድተዋል፡፡

በቀጣይም አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን የመሥራት እና ለነባሮቹ ጥበቃና እንክብካቤ የማድረግ ሥራ በትኩረት እንደሚሠራ አመላክተዋል፡፡

የአካባቢው ማኅበረሰብም የቱሪስቶችን ደኅንነት በመጠበቅ የክልሉ ታሪካዊና ባሕላዊ ቦታዎች እንዲጎበኙ በማድረግ ረገድ የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በሌላ በኩል በክልሉ ከነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ እስከ የካቲት ወር ድረስ በርካታ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ የአደባባይ በዓላት መኖራቸውን ገልጸው፤ በዓላቱን እሴታቸውን ጠብቆ በማክበር ቱሪስት እንዲገኝባቸው ይደረጋሉ ብለዋል፡፡

በተጠናቀቀው የ2016 በጀት ዓመት የክልሉን የቱሪስት መዳረሻዎች የማስፋፋትና ለቱሪስት ምቹ የማድረግ ሲሠራ መቆየቱን አስታውሰው፤ በተሠራው ሥራም በርካታ የውጭና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ክልሉን እንደጎበኙት በማድረግ ከሦስት ነጥብ 73 ቢሊዮን ብር በላይ መገኘቱን አስታውቀዋል፡፡

ክልሉ የቅዱስ ላሊበላ አብያተክርስቲያን፣ የጎንደር ቤተ መንግሥት፣ የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ በባሕርዳር ከተማ ዙሪያ ያሉ የጣና ገዳማትን ጨምሮ የበርካታ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ቦታዎች መገኛ በመሆኑ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኚዎች እንዲጎበኙ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ በመከፈቱ ምክንያት ብዙ የውጭ ኢንቨስተሮች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው በኢንዱስትሪ እና በማዕድን ልማት ሊሳተፉ የሚችሉበት ሰፊ ዕድል መኖሩን የሚናገሩት ምሁሩ፤ ይህም ለወጣቱ ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥር እንደሆነ ይገልጻሉ።

ከሰሞኑ ብሔራዊ ባንክ ያደረገው የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ ከዚህ በፊት የነበረውን የጥቁር ገበያን ሕገ ወጥ ሥራ የሚያስቆም በመሆኑ ትልልቅ የውጭ ሀገር ኩባንያዎች ገብተው በንግድ ሥራ እና በኢንቨስትመንት እንዲሠማሩ ዕድል ይሰጣል የሚሉት ምሁሩ፤ ይህም ከፍተኛ የሰው ኃይል ቅጥር የሚፈልግ በመሆኑ ለወጣቱ ጥሩ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር ይናገራሉ፡፡

ናይጄሪያ፣ ኬንያ፣ ግብጽ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ሴኔጋል ወጣቶች የፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ ተጠቅመው ከኢንተርኔት ጋር የተያያዘ ሥራ በመሥራት በርከት ያለ ካፒታል ወደ ሀገሮቻቸው ማምጣት እንደቻሉ አውስተው፤ በሀገራችንም የቴሌኮም ዘርፉ ነፃ ሆኖ እየመጣ በመሆኑ ወጣቶች ይህን በመጠቀም ትልቅ ሥራ ሊሠሩ እንደሚችሉ ይገልጻሉ፡፡

ማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው እንደ ሀገር መደረግ ከነበረበት ጊዜ ዘግይቶ ተግባራዊ የተደረገ ቢሆንም ኢኮኖሚው ላይ ትልቅ ለውጥ ለማምጣት ዕድል የፈጠረ መሆኑን ተናግረው፤ በኢትዮጵያ በአግሮ ኢንዱስትሪው፣ የውሃ ሀብት እና ሰፊ የእርሻ መሬት፣ ጥሩ መሠረተ ልማት በመገንባቱ እንዲሁም ከፍተኛ የወጣት ኃይል በመኖሩ ምክንያት ስኬታማ እንደሚሆን ይናገራሉ ፡፡

በተደረገው ማሻሻያ ኢትዮጵያ ያላትን ሀብቶች በማቀናጀት በብድር ሳይሆን በራሷ ምርታማነት የምትኖር አገር እንድትሆን ማድረግ ይቻላል ይላሉ፡፡

ናይጄሪያ እና ግብፅ በየዓመቱ ከ30 ቢሊዮን ዶላር በላይ ከዲያስፖራዎቻቸው ያገኛሉ የሚሉት ምሁሩ፤ ኢትዮጵያ ከዚህ አንጻር ሲታይ ከዲያስፖራዎቿ የምታገኘው በጣም አነስተኛ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ የጥቁር ገበያው ኢትዮጵያ ከዲያስፖራዎቿ ማግኘት የሚገባትን እንዳታገኝ ትልቅ እንቅፋት ሆኖ መቆየቱን የሚገልጹት ምሁሩ፤ በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ በገበያው እንዲወሰን የተደረገ በመሆኑ ኢትዮጵያ በቀጥታ ማግኘት የሚያስችላትን ጥቅም እንድታገኝ ዕድል እንደሚፈጥርም ይገልጻሉ፡፡ የኢኮኖሚው ዕድገትም በራሱ ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ትልቅ አስተዋፅዖ እንደሚኖረውም ይናገራሉ፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ስኬታማ እንዲሆን እየታዩ ያሉትን የሙስና ችግሮችን ማረም እንደሚያስፈልግ የሚናገሩት ቆስጠንጢኒዮስ (ዶ/ር)፤ በአገልግሎት አሰጣጥ በኩልም የሚታዩ ችግሮች ካልተፈቱ የውጭ አገር ኢንቨስተሮች መጥተው ሥራ ለመሥራት እንደሚቸገሩ ይገልጻሉ፡፡

ሙስና ብልሹ አሠራሮችን በማጋለጥ ረገድ ሚዲያዎች ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው የሚሉት ምሁሩ፤ የምርምራ ዘገባዎች ላይ በማተኮር የአገልግሎት አሰጣጡን ችግሮችን ማጋለጥ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋና የሥራ ዕድል እንዲበራከት መሥራት ይኖርባቸዋል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ሌላኛው የምጣኔ ሀብት ተንታኝ አቶ ሸዋፈራሁ ሽታሁን በበኩላቸው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ጠቃሚ እና አስፈላጊ ነው ይላሉ፡፡ መንግሥት ማሻሻያውን ከትክክለኛ ጊዜው ትንሽ ቀደም ብሎ እንደጀመረው የሚናገሩት ተንታኙ፤ የኅብረተሰቡ የመወዳደር አቋም እና የመንግሥት የውጭውን ዲፕሎማሲ የመቋቋም አቅም ሲዳብር ማሻሻያው ቢደረግ ይበልጥ የተሻለ ይሆን እንደነበር ይገልጻሉ፡፡

ማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ የውጭ ሀገር ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ካፒታላቸውን ካፈሰሱ መሠረታዊ የሚባሉ ፈተናዎች መካከል ከሆኑት መካከል ሥራአጥነት፣ የዋጋ ግሽበትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግርን የመፍታት ዕድል ይኖረዋል ነው ያሉት፡፡

አቶ ሸዋፈራሁ ወጣቶችም በተለይ በቱሪዝም፣ በኢንዱስትሪ፣ በባንክና በጅምላ ንግድ በሚፈጠረው የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገልጻሉ። ይህ ግን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በሌሎች ሀገራት ኢንቨስተሮች የካፒታል የመጥለቅለቅ ችግር እንዳያመጣ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበትም ይመክራሉ፡፡

ግብርናው ለአጠቃላይ የሀገሪቱ ምርት የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ከፍ ማለት እንዳለበት የሚገልጹት አቶ ሸዋፈራሁ፤ ኢትዮጵያ ለውጭ ሀገራት ልትሸጠው የምትችለው ነገር የግብርና ውጤቶችን በመሆኑ ግብርናው ላይ በማተኮር አርሶ አደሩን ማበረታታት እንደሚያስፈልግም ይገልጻሉ፡፡ ይህም ለወጣቶች የሥራ ዕድል የሚፈጥር ተጨማሪ መስክ ነው ይላሉ፡፡

መንግሥት የውጭ ምንዛሪ ጨረታ በማውጣት ለባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሲሰጥ በጥቁር ገበያ ላይ ያለውን የውጭ ምንዛሪ ስወራ ይቀንሳል የሚሉት ተንታኙ፤ ይህ የጥቁር ገበያውን አቅም በማዳከም ኢኮኖሚው ላይ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣም ይገልጻሉ፡፡

እንደ አቶ ሸዋፈራሁ በሕገወጥ መንገድ ሲሠራ የነበረው የጥቁር ገበያ አሁን በማሻሻያው በነፃ ገበያ ክፍት ሲደረግ የምርትና አገልግሎት ነፃነት ሊኖረው ይችላል፡፡ በኢትዮጵያ የአቅርቦት እና የፍላጎት መጠን የተጣጣመ ባለመሆኑ ኅብረተሰቡ ምርትና አገልግሎቱን ከቦታ ቦታ እንደፈለገው አንቀሳቅሶ በፈለገው ዋጋ እንዲሸጥ ሠላም እና መረጋጋት እንዲፈጠር መሠራት እንዳለበት የሚገልጹት ተንታኙ፤ ለተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው ይላሉ፡፡

የምጣኔ ሀብት ምሁራኑ እንደሚሉት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ትልቅ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ቢሆንም ስኬታማነቱ እንዲረጋገጥ በምሁራኑ እንደ ስጋት የተቀመጡት የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንቅፋት እንይሆኑ በትኩረት ቢሠራባቸው መልካም ነው ሲሉ ይመክራሉ፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት፤ ቱሪዝም በማነቃቃትና የባንክ ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪ በማድረግ ረገድ የሚፈጥረው ምቹ ሁኔታም ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን ነው የተገለጸው፡፡

# ሀገራዊ ምክክር ከሌሎች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በምን ይለያል? በሚሉት ነጥቦች ዙሪያ የሕግና የእርቀ ሠላም ባለሙያዎችን ጠይቀን ሃሳባቸውን ሰጥተውናል፡፡

ምክክር ማለት የተለያዩ ፍላጎቶች ሲስተዋሉ፣ ልዩነቶች ወደ ተካረረ መንገድ ሲያመሩ፣ ሀገራዊ የሆኑ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ሲያጋጥሙና በተደጋጋሚ ወደ ጦርነት የሚያስገቡ ምክንያቶችን በጋራ በንግግር ለመፍታት እንዲሁም የአቅጣጫ ለውጥ ለማምጣት የሚደረግ የሠላም ሂደት መሆኑን የእርቀ ሠላም ባለሙያና አማካሪ የሆኑት አቶ ጋረደው አሰፋ ይናገራሉ፡፡

ምክክር ዜጎች በአንድ ተቋም ጥላ ስር በመሆን ላጋጠማቸው ችግሮች በጥልቀት ተወያይተውና ተነጋግረው የመፍትሔ ሃሳብ እንዲያመነጩ የሚረዳ ተመራጭ የሠላም ሂደት እንደሆነ ይገልጻሉ።

ምክክር ውጤት ሳይሆን የሚያመጣው በምክክር ውስጥ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮችን የሚያመላክት ነው የሚሉት ባለሙያው፤ በምክክር እስካሁን ምላሽ ያላገኙና በሕዝብ መካከል መከፋፈል የፈጠሩ ጉዳዮችን መስመር በማስያዝ ቀጣይ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አለመግባባቶችን በዘላቂነት ይፈታል ሲሉም አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል ድርድር ከጦርነትና ወደ ጦርነት ከሚወስድ ውዝግብ ለመውጣት የሚደረግ የሰጥቶ መቀበል መርሕን የሚከተል የሠላም ሂደት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ለዚህም የፕሪቶሪያው የሠላም ስምምነት እንደ ማሳያ ያነሳሉ፡፡

ድርድር ሂደት በውስጡ ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን እንደሚይዝ የሚገልጹት አቶ ጋረደው፤ የመጀመሪያው ጦርነት በማቆም ወደ ተሻለ ሠላም መመለስ ሲሆን ሌላኛው ዳግም ወደ ጦርነት ላለመግባት ቃልኪዳን (ስምምነት) ማድረግን ይፈልጋል ይላሉ፡፡

እርቅ(ሽምግልና) ማለት ጦርነት በሌለበት ሁኔታ በታሪክ ሂደቶች፣ በተፈጠሩ ትርክቶችና በተለያዩ ምክንያቶች ማኅበረሰብ ተኳርፎ ሲቀመጥና ወደ አወንታዊ ሠላም ለመመለስ የሚረዳ ድልድይ መሆኑን አስገንዝበዋል። የኢትዮጵያ ባሕል የሚፈቅደው ማስታረቅንና ወደ ቦታው መመለስን እንደሆነ የሚያስረዱት አቶ ጋረደው፤ እርቅ (ሽምግልና) ሰዎች ከኩርፊያ ወጥተው አብሮ ወደሚሠሩበት ሁኔታ የሚያሸጋግር አፍሪካዊ እንዲሁም ሀገር በቀል ማኅበራዊ የሠላም ሥርዓት መሆኑን ያብራራሉ፡፡

በኢትዮጵያ የሚነሱ የመሬት፣ የሕገመንግሥት፣ የቋንቋ የመሳሰሉ ጉዳዮች ከታች ወደ ላይ እናምጣቸው ቢባል እድሜ ልክ በንትርክ ውስጥ ከመቆየቱ የተነሳ መፍትሔ ለማምጣት አዳጋች እንደሚሆን የሚጠቁሙት አቶ ጋረደው፤ ነገር ግን ምክክሩን የፖለቲካ፣ የሃይማኖት፣ የትምህርት ምሑራን እንዲሁም መገናኛ ብዙኃኖችን ጨምሮ መሰል አካላት አድርገውት ወደ ታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል እንዲወርድ የሚደረግና ከሞላ ጎደል ፖለቲካዊ የሚመስል የሠላም ሂደት እንደሆነ ይጠቁማሉ።

የኮሚሽኑ የተከተለው አካሄድ ከታችኛው የማኅበረሰብ ክፍል ወደ ምሑራን መሆኑን አንስተው፤ ይህም ሂደቱን እንዳይፋጥን ሊያደርገው ይችላል ሲሉ ስጋታቸውን ይገልጻሉ፡፡

ምክክር የብዙ ሰዎችን ተሳትፎ ቢጠይቅም ሁሉንም ሕዝብ ማመካከር በጣም አስቸጋሪ መሆኑን የሚያነሱት የእርቀ ሠላም ባለሙያው፤ ነገር ግን በመጀመሪያ ደረጃ ለተከሰቱ ችግሮች ዋነኛ ተዋናይ የሆኑ አካላት በጉዳዩ ላይ በጥልቀት እንዲመከሩበት ማድረግ ያስፈልጋል ነው የሚሉት፡፡

የኢትዮጵያ የሀገራዊ ምክክርም በዚሁ ሂደት ቢመራ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል የመፍትሔ ሃሳባቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

አቶ ፍቃዱ ጴጥሮስ ጠበቃና የሕግ ባለሙያ በበኩላቸው፦ ምክክር ማለት በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች ስለገጠማቸው የተለያዩ ችግሮች ምን ማድረግ እንዳለባቸው በጋራ የሚነጋገሩበት መድረክ ነው፡፡

ምክክር ከሌሎቹ የሠላም ግንባታ ሂደቶች አንጻር የሁሉንም ፍላጎት የሚንጸባረቅበት፣ ብዙ ተሳታፊና ረጅም ጊዜ ስለሚወስድ ወደሚፈለገው የጋራ ግብ ለመድረስ የሁሉንም ዜጎች አጀንዳ ማሰባሰብ እንደሚጠይቅ ይገልጻሉ፡፡

ላጋጠሙ ችግሮች ብቻ ለብቻ አስቀመጦ በማነጋገር መፍትሔ ማምጣት ሳይቻል ሲቀር ዜጎች ወደ ምክክር ሥርዓት እንደሚገቡ ይገልጻሉ፡፡

የምክክር ሂደት መግባባት ላይ የተመሠረተ ሲሆን በውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት ግልጽ በሆነ መንገድ ይቀመጣል፣ የሁሉም ዜጋ ተሳትፎ አለበት፣ በስተመጨረሻ ውጤቱም የሕዝብ ተቀባይነትን ያገኛል፡፡ ምክክር ሂደቱን ከሚያስተባበሩና ከሚያመቻቹ አካላት ውጪ ሌላ የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት የለበትም ይላሉ፡፡

ሂደቱን በምክክር ላይ አብዛኛው ነገር የጋራ መሆኑን የሚገልጹት አቶ ፍቃዱ፤ በመጀመሪያ ምክክር የሚፈልጉትን ነገሮች ግልጽ አድርጎ ማስቀመጥና መለየትን ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

ምክክር ላይ የሚቀመጡ አካላት በጋራ የሚፈልጉት ነገር እንዲታወቅ አጀንዳቸውን ሂደት ውስጥ ሁሉም ዜጋ በጋራ ማግኘት ወደሚፈልገው ነገር ለመድረስ ምን መደረግ አለበት ተብሎ የሚመከርበት ነው፡፡

ምክክር ትኩረቱ ሰቶ መቀበል ላይ ሳይሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ የጋራ መግባባትና ሠላም መፍጠር መሆኑን ጠቅሰው፤ ዋና ባሕሪው የጋራ መግባባት ለመፍጠር እንዴት እንሂድ የሚል ነው ብለዋል፡፡

ሌላኛው ድርድር ሲሆን ይህም ሰቶ መቀበል ላይ የተመሠረተ በመሆኑ እያንዳንዱ አካል አስቀድሞ ምን እንደሚቀበልና ምን እንደሚሰጥ ይታወቃል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ሂደቱ ከሞላ ጎደል ግልጽ ላይሆን ይችላል የሚሉት የሕግ ባለሙያው፤ በሂደቱ የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ይኖረዋል ብለዋል፡፡ በምክክርና በድርድር ውስጥ ጉዳዩን አድምጦ ውሳኔ የሚሰጥ አካል እንደማይኖር አስረድተዋል፡፡

ሽምግልና (እርቅ) ማለት በመቀያየም ወይም ባለመግባባት ውስጥ ያሉ ወገኖች ሀሳባቸውን ካቀረቡ በኋላ አሸማጋዮች በሚሰጡት የእርቅ ሀሳብ የነበሩ ችግሮች እንደሚፈቱ ገልጸዋል፡፡

# ከርምጃ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለመሆኑ መንግሥት በነጋዴዎች ላይ እየወሰደ ያለው ርምጃ ዘላቂ መፍትሔ ያመጣል ወይ? ስንል የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎችን ጠይቀናል።

የፐብሊክ ፖሊሲና ምጣኔ ሀብት ምሁሩ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ በአዲስ አበባ አብዛኛዎቹ ምርቶች የሚሸጡት ከጥቁር ገበያ በተገኘ ምንዛሪ ዋጋ ነው።

ይህም ማለት አንድን ዶላር በመቶ ሃያ ብር ገዝተው ከውጭ ሀገር ባመጡት ምርት ላይ ትርፋቸውን ጨምረው ምርቱን ለኅብረተሰቡ ያቀርባሉ ማለት ነው።

ከዚህ በመነሳት አሁን ላይ ነጋዴዎች የዋጋ ጭማሪ ማድረግ የለባቸውም ማለት ነው። የነጋዴዎች ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ የሕዝቡን ሠላም ይፈታተናል። በዚህም የመጀመሪያዎቹ ተጎጂዎች እነሱ ናቸው። መንግሥት ነጋዴዎች ላይ ከሚወስደው ርምጃ ባሻገር ሰፊ የማስተማር ሥራ ሊሠራ እንደሚገባ ያብራራሉ።

ሌላው መንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ከማሳወቁ በፊት መሠረታዊ ምርቶችን በብዛት ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባቱን መግለጽ ነበረበት ያሉት ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር)፤ ይህም ነጋዴዎች በመጋዘን ያስቀመጡትን ምርት አውጥተው እንዲሸጡ ያደርጋል ነው ያሉት።

አሁን ላይ መንግሥት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባቸውን ምርቶች ለሕዝብና ለነጋዴው እያሳወቀ መሆኑን የገለጹት ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር)፤ ይህ ተግባር ቀድሞ የተደረገ ቢሆን ኖሮ ውጤቱ መልካም እንደሚሆን ተናግረዋል። በዚህም ነጋዴው ከርምጃ ኅብረተሰቡ ደግሞ ከዋጋ ጭማሪ ይድን እንደነበር ይገልጻሉ።

ሕዝብን እየበዘበዙ እንዲሁም ራስን እያበለፀጉ የትም መኖር እንደማይቻል ለነጋዴዎች ማስተማር ይገባል። ሕዝብን የሚጎዳ ተግባር ማኅበራዊ ቀውስ የሚፈጥር እና እራሱን ነጋዴውን ፈተና የሚጥል መሆኑን ማሳወቅ ይገባል ብለዋል። ለዚህም የሚዲያ ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

ዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም የሰጡት የብድርና የድጋፍ ገንዘብ የኢኮኖሚ መሸጋገሪያ መሆኑን ገልጸው፤ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በሙሉ አቅማቸው ሲሠሩ እና የውጭ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ኢኮኖሚው ጠንካራ ይሆናል ባይ ናቸው።

ይህም የሥራ አጥ ቁጥርን ይቀንሳል። በዚህም የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ያድጋል። ይችን አጭር የውኸንብር ጊዜ መንግሥት ሊያደርግ የሚገባው ከሕዝብ ጥቆማ እየተቀበለ ቁጥጥሩን ማጠናከር አለበት። ለዚህም ከወረዳዎች፣ ከሲቪል ማኅበራትና ከሚዲያ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት አለበት ነው ያሉት።

ምክንያቱም አንዳንዴ ነጋዴዎች ሳያውቁ ሀገሪቱን ቀውስ ውስጥ ሊከቱ ይችላሉ። በዚህም ነጋዴው ተጎጂ መሆኑን ማሳየት ይገባል ያሉት ቆስጠንጢኖስ፤ ብዙ ሀገሮች የዋጋ ወሰን ያደርጋሉ። ለአብነት ሜክሲኮ ወደ 170 እቃዎች ላይ የዋጋ ወሰን አድርጋለች። ግብፅንም ብንመለከት ለሃምሳ ዓመት የዳቦ ዋጋ አልቀየረችም።

እነዚህንና መሰል ውሳኔዎችን መከተል የዋጋ ንረት ለመከላከል ይረዳል። ይህም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዳይጎዱ ያደርጋል ያሉት ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር)፤ በሀገራችን አሳታፊ እድገት እንዲመጣ ያደርጋል ብለዋል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ከቡር ገና፤ አለአግባብ ዋጋ በጨመሩ ነጋዴዎች ላይ እየተወሰደ ያለው ርምጃ ጊዜያዊ መፍትሔ እንጂ ዘላቂ መፍትሔ አያመጣም ባይ ናቸው። ነጋዴው የዋጋ ጭማሪ እያደረገ ያለው የውጭ ምንዛሪ የመግዣ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ነው ይላሉ። ይህንን ሁኔታ ለመከላከል በነጋዴዎች ላይ ርምጃ ሲወሰድ ይታያል ነው ያሉት።

ነጋዴው ካፒታሉን ካጣ ወደ ንግዱ በቀላሉ መመለስ ስለማይችል የሚወሰደው ርምጃ ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ሊሆን ይገባል ያሉት አቶ ከቡር ገና፤ ዘላቂ መፍትሔው ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት፣ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለውጭ ገበያ ምርቶችን በስፋት ማቅረብ መሆኑን ያብራራሉ።

የግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር ወደ ውጭ መላክ፣ በቂ መሠረተ ልማቶችን በማሟላት የውጭ ኢንቨስተሮችን መሳብ፣ የሀገሪቱን ሠላም መጠበቅ እና የሀገር ውስጥ አምራቾችን ማበረታታት ከርምጃው በሻገር ዘላቂ መፍትሔ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሕጋዊ ተቋማትን ውሳኔ አለማክበር ከሕዝብ ፍላጎት በተቃርኖ መቆም ነው!

የመላው ሕዝባችን የትናንት ሆነ የዛሬ የልብ መሻት ሰላም እና ልማት ነው፡፡ ይህ እንደ ሀገር ከመጣንበት ብዙ ዋጋ ካስከፈለን እና እያስከፈለን ካለው የግጭት ፣ የኋላቀርነት እና የድህነት ታሪክ ለዘለቄታው ለመውጣት ከመፈለግ የሚመነጭ ፤ተጨባጭ እስካልሆነ ድረስ የመጪዎቹ ትውልዶችም መሻት ሆኖ የሚቀጥል ነው፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመን የሀገረ- መንግሥት ግንባታ ታሪክ ካላቸው ጥቂት የዓለም ሀገራት በዋነኛነት የምንጠቀስ ፤ በነዚህ ረጅም ዓመታትም የታላላቅ ስልጣኔዎች ፣የብዙ ታሪክ እና ባህል ባለቤት በመሆን፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እና ሞገስ ማግኘት የቻልን፤ የሰው ልጅ መገኛ በመሆንም ተጠቃሽ ነን፡፡

ይህም ሆኖ ግን እንደሀገር በየዘመኑ እያጋጠመን ካለው የሰላም እጦት ፣ ከዚህ ከሚመነጭ ድህነት እና ኋላቀርነት የተነሳ፤ በአብዛኛው መታወቂያችን ጦርነት ፣ ጦርነት የሚፈጥረው ሁለንተናዊ ጉስቁልና እና ተመጽዋችነት ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ በዚህም የታሪካችንን ያህል ቀና ብለን እንዳንሄድ ሆነናል፡፡

በአንድ በኩል ከቀደሙ የግጭት ታሪኮቻችን/ ስህተቶቻችን በአግባቡ መማር አለመቻላችን፣ ከዚያም ባለፈ ችግሮቻችንን ዘመን በሚዋጅ የአስተሳሰብ መሠረት ላይ ቆመን ለመፍታት የሚያስችል ዝግጁነት አለመፍጠራችን ፣ እንደ ሕዝብ የምንመኘውን ሰላም እና ልማት እውን ማድረግ ሳይቻለን ቀርቷል፡፡

እንደ ጥላ እየተከተለን ያለውን ይህንን ችግር አሸንፎ ለመውጣት በተለያዩ ዘመናት የነበሩ ትውልዶች ከፍ ባለ የለውጥ መነቃቃት ተነሳስተው፤ የተስፋ መዝሙር እየዘመሩ ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል ፤ለዚህ የለውጥ /የመለወጥ ድምጽ ጎልቶ የተሰማባቸውን ታሪኮቻችንን ማየት በራሱ ከበቂ በላይ ነው፡፡

የነዚህ ትውልዶች የለውጥ መነቃቃት በተለያዩ የቡድን እሳቤዎች እና እሳቤዎቹ በሚፈጥሯቸው ተቃርኖዎች ተጠልፈው፤ ሀገር እንደ ሀገር ተስፈኛ ትውልዶችን ከማጣቷ ባለፈ፤ ትውልዶቹ የተመኙትን በብዙ መነቃቃት ዋጋ የከፈሉበት ሀገራዊ ሰላም እና ልማት /ብልጽግና እውን መሆን ሳይችል ቀርቷል፡፡

በተስፈኛ ትውልዶች መቃብር ላይ የሚመሰረቱ የፖለቲካ ሥርዓቶችም፤ ሀገርን ወዳልተገባ ተቃርኖ እና የግጭት አዙሪት ውስጥ ከመክተት ባለፈ ሀገርን ከትናንት ጥፋቶች በመታደግ ፣ ወደ አዲስ የለውጥ / የመለወጥ የታሪክ ምዕራፍ ማሸጋገር ፣ በዚህም ለሀገር እና ለሕዝብ መሻት ተጨባጭ ምላሽ መሆን አልቻሉም፡፡

ለዚህ ደግሞ ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት ያለውን የሀገራችንን የለውጥ ታሪክ መመልከት ፤በዚህ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ በቡድኖች መካከል የተፈጠረ ተቃርኖ ፣ ሀገር እና ሕዝብን የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለ ፣ ችግሩ አድጎ ትናንት የሀገር ህልውና ስጋት ሆኖ እንደነበርም መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

ይህንን ችግር ለዘለቄታው ለመፍታት ከሁሉም በላይ ከትናንት ስህተቶቻችን መማር ፣ ችግሮችን በቀደመው የኃይል አሰላለፍ ትምክህት ፣ የአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት ለመፍታት ከመሞከር ታቅቦ፣ በውይይት እና በድርድር ፣ ህግ እና ህጋዊነትን መሰረት ባደረገ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል የፖለቲካ ባህል ማጎልበት ወሳኝ ነው፡፡

የለውጥ ኃይሉ ወደ ስልጣን ከመጣ ማግስት ጀምሮ እንደ ሀገር ይህንን አዲስ የፖለቲካ ባህል ተግባራዊ ለማድረግ የሄደበት መንገድ በብዙ ፈተናዎች የታጀበ ፣የለውጡ የጉዞ ፍጥነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የፈጠረ ቢሆንም፤ ከትናንት ተምሮ ለሕዝባችን የሰላም እና የልማት መሻት እውን መሆን የሚኖረው ስትራቴጂክ አስተዋጽኦ አልፋ እና ኦሜጋ ነው፡፡

አንዳንድ ኃይሎች ቀደም ሲል ከፌዴራል መንግሥት ጋር የገቡበትን ችግር በሰለጠነ መንገድ ፣ በሰላማዊ ውይይት እና ድርድር ለመፍታት አለመቻላቸው በአጠቃላይ ሀገርን ፣ ከሁሉም በላይ ሕዝብን ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለው ፣ ችግሩ በድርድር በሰላም ስምምነት መቋጨቱ የቱን ያህል እፎይታ ይዞ እንደመጣ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የዘመናት መሻቱ ሰላም እና ልማት ነው፡፡ እስከ ዛሬ የከፈላቸው መስዋእትነቶችም ይህንን እውነታ ተጨባጭ ለማድረግ የተከፈሉ ናቸው፡፡ የትኛውም ለሕዝብ ፍላጎት እታገላለሁ የሚል ኃይል ለዚህ የሕዝቡ ፍላጎት ተገዥ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

ሰላም እና ልማት የሚመነጨው ለሕግ እና ለሕግ የበላይነት የተገዛ ማኅበረሰብ ማፍራት ሲቻል ነው፡፡ ችግሮችን በውይይት እና በድርድር በሰላማዊ መንገድ መፍታት የሚያስችል የፖለቲካ ሥርዓት መፍጠር ሲቻል ነው፡፡ ይህም የትናንት ስህተቶቻችንን በዘላቂነት ማረም የሚያስችል ብቸኛው መንገድ ነው ፡፡

ከዚህ አኳያ ማንኛውም የሕዝብ ፍላጎት ፍላጎቴ ነው የሚል አካል ሕግ እና ሕጋዊ ሥርዓትን ማክበር ፣ልዩነቶችን በውይይት እና በድርድር መፍታት ፣ ከሁሉም በላይ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸውን ተቋማት ውሳኔ ማክበር ፣ ለውሳኔያቸው ተፈጻሚነት ራሱን ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ውጪ በሕዝብ ስም የሚደረግ የትኛውም እንቅስቃሴ ከሕዝብ ፍላጎት ጋር ተቃርኖ መቆምን በተጨባጭ አመላካች ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## “የትርክት ዕዳና በረከት” መጽሐፍ ላይ የቀረበ ዳሰሳ

- የመጽሐፉ አዘጋጅ፡- ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፤
- የኅትመት ዘመን፡- 2016 ዓ.ም.
- የገጽ ብዛት፡- 575 ገጽ
- የወረቀት መጠን(ሳይዝ)፡- በሸሮ መልክ A5 ወረቀት፣
- የመሸጫ ዋጋ፡- ብር 1000.00 (አንድ ሺህ ብር)፤
- ታተመ፡- ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፤

“የትርክት ዕዳና በረከት” በሚል ርዕስ ለንባብ የበቃው መጽሐፍ፤ በስድስት ክፍሎች የተደራጀ እና በ48 ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው:: አንድም መጽሐፍ ለመረዳት ርዕስ ትልቁ የመግቢያ በር ነው:: ከዚህ አኳያ ከታየ፤ የመጽሐፉን ርዕስ አጠቃላይ የመጽሑፉን ጭብጥ የተሸከመ ሲሆን፤ ከርእሱ ለመረዳት የሚቻለውም በኢትዮጵያ ሲነገር የኖረው ትርክት እንደ ሀገርም ሆነ ሕዝብ ዕዳም፣ በረከትም ያስከተለ መሆኑን ነው::

አንባቢም ከመጽሐፉ ርዕስ የተረዳውን ሃሳብ ይዞ የመጽሐፉን ገጾች ዘልቆ ሲያነብም፤ ትርክት ጠቀሜታው እና ዘላቂነቱ ታስቦበት በዓላማ ከተዘጋጀ ለሀገር መድህን ስለመሆኑ ያስገነዝቡታል:: በአንጻሩ፣ ከሀገር እና ከወገን ዘላቂ ጥቅም ይልቅ ለግል እና ለቡድኖች ጊዜያዊ ጥቅም ተብሎ ከተዘጋጀ፣ ትርክት ለሀገርም፣ ለሕዝብም ዕዳ ይዞ እንደሚመጣ ነው ከመጽሐፉ ገጾች የሚረዳው::

ይሄን የትርክት ዕዳነትም ሆነ በረከትነትን ከመግለጥ አኳያ፣ የመጽሐፉ ገጾች የሚያብራሩበት የራሳቸው አወቃቀር አላቸው:: ለዚህም ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት፣ በስድስት ክፍሎች የተደራጁ 48 ምዕራፎች በየፈርጃቸው የትርክትን ዕዳነትም፣ በረከትነትም ለማስረዳት ተሰናድተዋል::

በክፍል አንድ- የኢትዮጵያ ፖለቲካ ትርክት ማጠንጠኛዎችን፤ በክፍል ሁለት- ነገረ ሕወሓትን፤ በክፍል ሦስት- ነገረ “ጃውሳ”ን፤ በክፍል አራት- ነገረ አነግን፤ እንዲሁም በክፍል አምስት ቀደምት የኢትዮጵያ ሥልጣኔ መልኮችን አስነብቧል:: የመጨረሻው ክፍል ደግሞ ሀገራችን የገጠሟት የተቃርኖ ትርክቶች መፍትሔ የሚያገኙበትን መንገድ አመላክቷል::

መጽሐፉ፣ በዚህ መልኩ ተደራጅተው በቀረቡት ክፍሎቹ ባሉ ምዕራፎች ታግዞ፤ በ1960ዎቹ በነበሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሲቀነቀን ኖሮ፣ መጨረሻም ሀገር እንድትመራበት ተዘጋጅቶ የቀረበው የተዛነፈ ትርክት ያስከተለውን ዕዳ፤ ስለ ገዥና ተገዥ የተሰጠ የተጣመመ ትርጓሜ ሀገራችን ለገጠማት ችግር ከፍተኛውን ሚና መጫወቱን ያብራራል::

በተለይ ከአለፉት ኀምሳ እና ስልሳ ዓመታት ጀምሮ ሲዘራ የኖረው የተሳሳተ የፖለቲካ ትርክት፤ ከፅንሰት እስከ ፍሬ ያሳየውን ዕድገት፣ የትርክቱ ፍሬዎች የፈጠሩትን ዕዳ፣ እንዲሁም ከተሳሳተው ትርክት ለመውጣት ሊከናወኑ ስለሚገባቸው ተግባራት ተንትኖ አቅርቧል::

“የሀገራዊ ትርክት ከትናንት እስከ ዛሬ” በማለት በሚጀምረው ምዕራፍ፤ ጸሐፊው መልካምም፣ እኩይም የሚላቸው ትርክቶች ምንጫቸው ከየት እንደሆነ ዳስሷል፤ እነዚህ እኩይ ትርክቶች አድገው ለፍሬ መብቃታቸውን አብራርቷል:: ትርክቶቹ ቅቡልነት እንዲያገኙ እድል የሰጡ ሽንቁሮች (መጠጊያ ምክንያቶች) መኖራቸውንም ገልጿል::

ለአብነት፣ ሀገር ለመምራት ቅቡልነት የማግኘት ፍርሃት የነበረበት ድርጅት፣ ለሥልጣን ሲበቃ የማይገናኙ ነገሮችን በማገናኘት አንድን የማኅበረሰብ ክፍል የመሥዋዕት ፍየል አድርጎ ማቅረቡን አመላክቷል:: የእንዲህ ዓይነቱን ፖለቲካዊ ዕሳቤ ደግሞ፣ ቅቡልነትን ያስገኝልኛል በሚል ምክንያት የመረጠበት የመጀመሪያው ነጥብ፣ የቀደመ ቁስልን መቀስቀስ መሆኑን፤ ይሄን መሰል አካሄድ ደግሞ በሌለ ጭራቅ ሌሎችን አስፈራርቶ የራሱ ተከታይ የማድረግ ሙከራ ስለመሆኑ ጸሐፊው ያስረዳል፤(ዳንኤል፣ 2016፣ 23)::

በዚህ መልኩ ጊዜያዊ ቅቡልነት ለማግኘት የሚፈጸም እንዲህ ያለ ትርክት እና ድርጊት ሀገራችንንም፣ ሕዝቦቿንም ዋጋ እያስከፈላቸው መሆኑን ጸሐፊው ደጋግሞ በገለጸበት በዚህ መጽሐፍ፤ ጠባብ፣ ትምክህት እና ነፍጠኛ የሚሉ ሦስት ስያሜዎችም በወቅቱ ጊዜያዊ ቅቡልነትን ለማግኘት ሲባል ለተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች መገለጫ ሆነው እንዲሳሉ ተደርገው የተሰጡ መሆናቸውንም አመላክቷል ::

ጸሐፊው፣ “እነዚህ ሦስት ስያሜ ቃላት ወደ ፖለቲካችን የገቡበት መሠረታዊ ምክንያት ሁለቱን የኢትዮጵያ ታላላቅ ብሔሮች አግልሎና አጋጭቶ ለመኖር ነው፤” (ዳንኤል፣ 2016፣ 28)፤ በማለት የስያሜዎቹን አመጣጥ ይተነትናል::

> ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ጊዜ የታሪክ ሙግቶች ከትናንት ይልቅ በዛሬ የተመሠረቱ ናቸው:: ክርክሩ ትናንት ያ ድርጊት በመደረጉ የሚመጣ ሳይሆን፤ ዛሬ ያንን ድርጊት በምንመለከትበት መነጽር የተነሣ የሚመጣ ነው

ስያሜዎች ፤ ይገዳደሩኛል ወይም ሥልጣን ይቀናቀኑኛል በማለት የሚፈራቸውን ብሔሮች እያጋጨ ለመኖር የተፈበረኩ መሆናቸውን ይገልጻል::

እነዚህ ደግሞ ሀገርንም ሆነ ሕዝብን ከፍ ላለ ችግር ያጋለጡ መሆናቸውን በመጥቀስ፤ በቀጣይ እንዲህ ያለው ፍረጃ በሀገር ላይ ያስከተለውን መዘዝ በሚገባ በመረዳት ጊዜያዊ ጥቅም ለማግኘት ተብሎ በሀገር ላይ ዘላቂ ጥፋት ከሚያስከትል እኩይ ድርጊት መቆጠብ የሚገባ መሆኑን ያሳስባል:: ቀደም ብለው የተፈጠሩ እኩይ ትርክቶች ያስከተሉትን ዕዳ ወደ በረከት ለመቀየር መሥራት እንደሚያስፈልግም ጸሐፊው ጠቁሟል::

ጸሐፊው፣ የትርክት እዳን ወደ በረከት ለመቀየር ከሚያግዙ ጉዳዮች መካከል ሲጠቅስ፤ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በየዘመናቱ ያሳየውን ዕድገትና የቀለማት መቀያየርን ያስተናገደ ስለመሆኑ ገልጿል:: የአሁኗ ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት ሰንደቅ ዓላማ ከመቼ ጀምሮ አገልግሎት ላይ እንደዋለም ጸሐፍትን አስረጂ በመጥቀስ ተንትኖ አቅርቧል:: በመቀጠልም የሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ በምክክር ሊፈታ እንጂ ጦር ሊያማዝዝ እንደማይገባ መፍትሔ ይሆናል ብሎ ያመነበትን አጋርቷል::

የታሪክ አጻጻፍን በተመለከተም፣ ስለታሪክ አጻጻፍ የታሪክ ምሁሩን ክርስቶፈር ክላፋምን ጠቅሶ፤ “ታሪክ በዛሬው አመለካከት ላይ ተመሥርቶ ስለትናንት የሚነገር ትርክት ነው:: የዛሬ አመለካከት በተቀየረ ቁጥር የታሪክ ትርክትም ይቀየራል:: ምክንያቱም ምንም እንኳን ትናንትን ለመቀየር ባንችል ዛሬ የሚቀያየረው አመለካከታችን ስለ ትናንት የተለያዩ ጥያቄዎችን እንድናነሣ ያደርገናል፤” ይላል::

“ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ጊዜ የታሪክ ሙግቶች ከትናንት ይልቅ በዛሬ የተመሠረቱ ናቸው:: ክርክሩ ትናንት ያ ድርጊት በመደረጉ የሚመጣ ሳይሆን፤ ዛሬ ያንን ድርጊት በምንመለከትበት መነጽር የተነሣ የሚመጣ ነው:: የሰው ልጅ አመለካከት እስከተለወጠ ድረስ በታሪክ ላይ የሚኖረን ክርክር መቼም ቢሆን ይኖራል፤” (ዳንኤል፣ 2016፣ 70-71)፣ በማለት የራሱን ሃሳብ አካፍሏል::

ትናንትን በዛሬ መነጽር ማየት ሀገራችንንም ሕዝቧንም ዋጋ እያስከፈለ መሆኑን፤ ትናንት በተፈጸመው ዛሬን ለመበየን መነሣታችን፣ ለንትርክ የሚጋብዘን መሆኑን የታሪክ ምሁሩን ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴን ጠቅሶ፤ “በዓለም ላይ የኢትዮጵያውንን ያህል በታሪክ ጉዳይ የተያዙ ሕዝቦች በጣም ጥቂቶች ናቸው፤” (ገጽ 571)፣ በማለት ገልጾታል:: ይሄ አገላለጽ የሚያመለክተው፤ ታሪክን ለራሳችን በሚመች መልኩ ብያኔ እየሰጠን መጠቀማችን ዋጋ እያስከፈለን ስለመሆኑ ነው::

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

አዲስ ዘመን | ረቡዕ ነሐሴ 8 ቀን 2016 ዓ.ም



# በገቢ ግብር ውዝግብ ምክንያት ሊበተን ጫፍ የደረሰው የቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን

**በመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ቡድን**

የዛሬው የፍረዱኝ ዓምድ ዝግጅታችን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ቤንች ሸኮ ዞን በሚገኘው የቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች ዩኒየን እና በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርንጫፍ መካከል የተፈጠረ ውዝግብ ያስመለክተናል።

የቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን ለበርካታ ዓመታት ከአርሶ አደሩ ቡና እና ቅመማ ቅመሞችን በመሰብሰብ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ ሲያርብ ቆይቷል። በነበረውም ቆይታ አርሶ አደሮችን እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያን በማገናኘት የድልድይነት ተግባር ሲያከናውን ቆይቷል። ከሽያጭ የሚያገኘውን ገንዘብ ምንም አይነት የግብር ክፍያ ሳይቆርጥ ለአርሶ አደሮች ሲያከፋፍልም ነበር። ነገር ግን የጅማ የገቢዎች ቅርንጫፍ ዩኒየኑ በራሱ ገበያ አፈላልጎ እንደሸጠ በማድረግ ከህግ ውጪ ግብር እንድንከፍል ጠይቆናል።

ከመጠየቅም ባለፈ የዩኒየኑን እና የሥራ አስኪያጁን የባንክ ሂሳብ ዘግቶ ዩኒየኑ ምንም አይነት ስራ መስራት እንዳይችል ሆኗል። በዚህም ዩኒየኑ ለከፍተኛ ኪሳራ ከመጋለጡም ባለፈ ለመፍረስ ተቃርቧል። በገቢዎች ላይ የተጸመብንን በደል የኢትዮጵያ ህዝብ አይቶ ይፍረደን" ሲሉ የዩኒየኑ ሥራ አስኪያጅ ጌታሁን ተክሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ቡድን አቤት ብለዋል።

የመልካም አስተዳደር እና የምርመራ ቡድኑም የኢትዮጵያ ህዝብ ግራ ቀኙን አይቶ መፍረድ ይችል ዘንድ ከሰዎች እና ከሰነዶች ያገኛቸውን መረጃዎች በሚከተለው መልኩ አጠናክሮታል።

ከአቤቱታ አቅራቢው አንደበት

እንደ አቶ ጌታሁን ገለጻ፤ የቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች ዩኒየን ከ2ሺ በላይ አባላትን በውስጡ የያዘ በ14 መሰረታዊ ማህበራት በ1997 ዓ.ም የተመሰረተ ነው። መነሻ ካፒታሉም ሁለት መቶ 10 ሺህ ብር ነበር። ከአቶ ጌታሁን ተክሌ በፊት ዩኒየኑ አራት ሥራ አስኪያጆች የመሩት ሲሆን፤ አቶ ጌታሁን አምስተኛ ሥራ አስኪያጅ ናቸው። እርሳቸው ሥራ አስኪያጅ ሆነው ከመምጣታቸው በፊት ዩኒየኑ ያን ያህል ትርፋማ እንዳልነበር በማስረጃዎች አስደግፈው ይናገራሉ።


በ2003 ዓ.ም ላይ ዩኒየኑ በጣም ከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቆ እንደነበር የሚናገሩት አቶ ጌታሁን፤ በወቅቱ መንግሥት ባደረገው ከፍተኛ ድጋፍ ከመዘጋት መዳኑን ይገልጻሉ። በ2003 ዓ.ም በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ከፍተኛ የሆነ የማህበራት ንቅናቄ መደረጉን ተከትሎ በ2004 ዓ.ም የቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው መቀጠራቸውን ያስረዳሉ።

እንደ አቶ ጌታሁን ገለጻ፤ የይርጋ ጨፌ፣ የኦሮሚያ እና የሲዳማ ቡና አምራች ገበሬዎች የህብረት ስራ ዩኒየኖች በሀገር አቀፍ ደረጃ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ዩኒየኖች ናቸው።የቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች ዩኒየንም በእነዚህ ዩኒየኖች ልክ በሀገር አቀፍ ደረጃ ታዋቂ መሆኑን አመላክተዋል።

እንደሀገር ከሚገኙ ትልልቅ ዩኒየኖች መካከል የኦሮሚያ ዩኒየን በቀዳሚነት እንደሚቀመጥ የሚናገሩት አቶ ጌታሁን፤ ሲዳማ በሁለተኝነት እንደሚከተል፤ የይርጋጨፌ እና ቤንች ማጂ እየተቀያየሩ ሶስተኛ እና አራተኛ ደረጃን እንደሚይዙ ይናገራሉ። በተጨማሪም በሀገሪቱ ከሚገኙ አጠቃላይ 496 የቡና ነጋዴዎች ውስጥ 29ኛ እንደነበር ጠቁመዋል።

ከላይ የተጠቀሱት ጨምሮ በሀገራችን የሚገኙ የበርካታ የህብረት ስራ ዩኒየኖች ቦርድ ሰብሳቢ መሆናቸውን የሚናገሩት አቶ ጌታሁን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርንጫፍ አካውንቱ ተዘግቶ ከስራ እንቅስቃሴ ውጭ ከመሆኑ በፊት የቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን እንደሀገር በከፍተኛ የስራ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደነበር ያስረዳሉ።

ህብረት ስራ ዩኒየኑ ከስራ ውጪ የተደረገው በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ግጭት በተፈጠረበት ወቅት



የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
SOUTHWEST ETHIOPIA PEOPLES REGIONAL STATE COOPRATIVE DEV'T AGENCY

ቁጥር / Ref. NO ህስልኤ/00381/08
ቀን / Date 06/11/2015ዓ.ም

ለኢትዮጵያ ህብረት ስራ ኮሚሽን
አ.አ


ጉዳዩ:- **የድጋፍ ደብዳቤ ስለመስጠት፣**

ከላይ በርእሱ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ የቤንች ማጅ ጫካ ቡና አምራቾች ኃ/የተወሰነ ህ/ሥራ ዩንዬን በገጠመዉ የታክስ እዳ ክስ ምክንያት ከኤጀንሲያችን ለኢ/ያ ህ/ስራ ኮሚሽን በተጻፈዉ የድጋፍ ደብዳቤ መነሻነት እና ኮሚሽኑ ባደረገዉ ቀና ትብብር ጉዳዩ ለፌደራል ገንዘብ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ቀርቦ በአዋጅ በተሰጠዉ ስልጣን እርከን ዉስጥ ያለዉን ወለድና ቅጣት ቀሪ በማድረግ ፍሬ ግብሩ እንዲከፈል ለገቢዎች ሚኒስቴር ቁጥር ታ/ክ//ቀ/5/410 በቀን 17/08/2015 ዓ.ም በጻፈዉ ደብዳቤ ማሳወቁን በመግለጽ በገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርጫፍ ጽ/ቤት አ/ገ/ሚ/110.263/15 በቀን 28/08/2015ዓ.ም በጻፈልን ደብዳቤ ገልጾልናል። ምንም እንኳን ገንዘብ ሚኒስቴር ፍሬ ግብሩን ብቻ ዩኒየኑ እንዲከፍል የወሰነ ቢሆንም ዩኒየኑ ከ2 አመት በላይ በአካዉንት መዘጋት ምክንያት ከግቢይት ስራዉ ተፈናቅሎ በመቆየቱ በተቋሙ፣ በሰራተኛዉ፣ በስሩ ባሉት መ/ማህበራትና በአባላቱ ላይ ያደረሰዉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ባሻገር ላላስፈላጊ የባንክ ወለድና ቅጣት በመዳረጉ የደረሰበትን ከፍተኛ ጉዳት የመጣዉ በኢፌዲሪ ህ/ስራ አዋጅ 985/2009 ዓ.ም መሰረት ዩኒየኑን ኦዲት የማድረግ ስልጣን የተሰጠዉ በየደረጃዉ ያለዉ የህብረት ስራ ተቋም ሆኖ ሳለ ገቢዎች በአዋጅ ባልተሰጠዉ ስልጣን ምንም አይነት የኦዲት የማድረግ ጥያቄ ሳያቀርብ ምርመራ ላድርግ ነዉ በሚል ምክንያት ለዩኒየኑ ኃላፊዎች በቀረበዉ ጥያቄ የዩኒየኑን ሰነድ ወስዶ ያገኘዉን የኦዲት ግኝት ህግና አሰራርን ከለመከተሉም በላይ ዩኒየኑ አለመቀበሉንና ቅሬታንም ለሚመለከታቸዉ የመንግስት ተቋማት ሁሉ በማሳወቅ ችግሩ ዘለቄታዊ መፍትሄ እንዲኖረዉ እንዲደረግ አቤቱታዉን አቀርቧል። ከዚህም ባሻገር ለቀድሞ ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ጉዳዩ ይመለከተን እደሆነ በደብዳቤ ጠይቀን እንደማይመለከተን በቁጥር ግህብ/አ14/1/538/07 በቀን 16/03/05 የገለጸልን ሲሆን የዩኒየኑ አካዉንት ታግዶ የግብይት ስራችን እስከቆመበት 2013 ዓ.ም ድረስ በተደረገ የህብረት ስራ ኦዲት ግኝት ያልተገኘና መሰብሰብ ያለብን ስለመሆናችን ያሳወቀንም አካል ባልነበረበት ሁኔታ ባልተሰጠዉ ስልጣን የጅማ ድስትሪክት የገቢዎችና ጉምርክ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኦዲት ግኝት አግኝቻለዉ በሚል ያልተሰበሰበ ገንዘብ መሰብሰብ ነበረበት በሚል ብቻ የቀረበዉ **የእዳ ጥያቄ ለአባላቱ እና ለሀገሪቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተና በማበረከት ላይ ያለዉን ዩኒየን በህልዉናዉ እንዳይቆይ የሚያደርገዉ በመሆኑ** የተጣለብን ከ22,541,03.90(ሃያ ሁለት ሚሊዮን አምት መቶ አርባ አንድ ሺ ሶስት ብር ከዘጠና **ሳንቲም) ፍሬ ግብር** እንዲከፍል መጠየቁ የተቋሙን ህልዉና መልሶ ለአደጋ የሚያጋልጥ በመሆኑ ኤጀንሲዉ **ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ህብረት ስራ ኮሚሽን በሚከተሉት አጀንዳዎች ላይ ማለትም:-**

**1ኛ. በገቢዎች ሚኒስቴር እንዲከፈል በመጠየቅ ላይ ያለዉ** ከ22,541,03.90 (ከሃያ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ **አንድ ሺ ሰላሳ አራት ብር ከዘጠና ሳንቲም** ) በላይ ቀሪ ፍሬ ግብር ክፍያ ስልጣን በተሰጠዉ በህብረት ሥራ ኦዲተር

Website: http://www. E-mail:

ፖ.ሣ.ቁ. P.O.Box. | ስ.ቁ. TEL. | ፋክስ Fax | ሚዛን-ኢትዮጵያ ሚዛን-አማን ETHIOPIA



ኦዲት ያልተደረገና ኦዲት ለማድርግ ያልተሰጠዉ አካል ኦዲት አድርጎ ያገኘሁት ግኝት ነዉ ብለዉ በራሱ ያቀርበ መሆኑ ታዉቆ ቀሪ የተባለዉ ዕዳ ዉድቅ እንዲደረግ።

2ኛ. ዩኒየኑ ጥራቱን የጠበቀ ምርት አሰራር ጠብቆ ወደ ዉጭ ልኮ የተፈፀመ ግብይትበገኘዉ ምክንያት በተፈጠሩ ስተቶች ምክንያት ክፍያ ሳይከፍል ቀርቶ ዩኒየኑ ለዉጭ ጉዳይ ያመለከተ ቢሆንም እልባት ባለማግኘቱ ምክንያት የዘገየዉ የአንድ ኮንቴነር ቡና ገንዘብ ገዠዉ ያለመክፈሉ ጉዳቱ ዩኒየን ና የዩኒየኑን አባላት ብቻ ሳይሆን የገሪቱን መንግስትና ህዝብንም የሚጎዳ በመሆኑ ከሚመለከተዉ ጋር በመነጋገር ያልተከፈለልን ክፍያ የምከፈልበት መፍተሄ ይፈለግልን በማለት የቤንች ማጅ ጫካ ቡና አምራቾች ኃ/የተወሰነ ህ/ሥራ ዩንዬን የድጋፍ ደብዳቤ እንድፅፍ ጠይቆዉናል።

በመሆኑም የቤንች ማጅ ጫካ ቡና አምራቾች ኃ/የተወሰነ ህ/ሥራ ዩንዬን ከዚህ ቀደም ባደረገዉ እንቅስቃሴ ለአባላትም ሆነ ለሀገሪቷ የራሱን አስተዋጽኦ እያደረገ የቆዬ ስሆን አንዳአንድ ከአገባብ ዉጭ እየደረሰበት ባለዉ ተጽህኖ ወደ ኃላ እንዳይመለስ ታሳብ በማድረግ፤

1ኛ.ለህብርት ሥራ ማህበራት የወጣ አዋጅ ቁጥር 985/2009 በአንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ህብረት ሥራ ማህበራቶችን ኦዲት የሚደረጉት በአደራጀዉ ህብረት ሥራ ተቋም በህብረት ሥራ ማህበራት ኦዲተሮች መሆን እየታወቀ ባልተሰጠዉ ስልጣን የጅማ ድስትትርክት የገቢዎችና ጉምርክ ባለስልጣን ዩኒዬናችንን በራሱ ፍቃድ ገቢቶ ኦዲት በማድርግ ያለአገባብ 22,541,03.90 (ከሃያ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ አንድ ሺ ሰላሳ አራት ብር ከዘጠና ሳንቲም ) በላይ ቀሪ ፍሬ ግብር ክፍያ ቀሪ ዕዳ አለ ማለቱ ከስልጣኑ ዉጭ ያደረገዉ ኦዲት መሆኑ ታዉቆ ህግና አሠራርን የተከተለ ምላሽእንድሰጣቸዉ ።።

2ኛ.ዩኒየኑ ጥራቱን የጠበቀ ምርት አሰራር ጠብቆ ወደ ዉጭ ልኮ በገኘዉ ምክንያት በተፈጠሩ ስተቶች ምክንያት ክፍያ ሳይከፍል ቀርቶ ዩኒየኑ ለዉጭ ጉዳይ ያመለከተ ቢሆንም እልባት ባለማግኘቱ ምክንያት የዘገየዉ የአንድ ኮንቴነር ቡና ገንዘብ ገዠዉ ያለመክፈሉ ጉዳቱ ዩኒየንና የዩኒየኑን አባላት ብቻ ሳይሆን የገሪቱን መንግስትና ህዝብንም የሚጎዳ በመሆና ለወደፊቱ ለምደረጉት የንግድ ልዉዉጥ ስርዓትም መጥፎ ምሳሌ ሆኖ እንዳይለመድ በዓለም የንግድ ዉል መሠረት ለመገበያየት የገቡት ዉል መፈጸም ስላለበት የኢ.ት.ጵያ ህ/ሥራ ኮሚሽን ከሚመለከተዉ አካላት ጋር በመነጋገር መንግስታት ለመንግስታት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በማድረግ ዩኒየኑ ክፍያ እንዲያገኝ እንዲደረግ ተገብዉን ድጋፍና ትብብር በኮሚሽኑ ይደረግላቸዉ ዘንድ እንጠይቃለን።

ከሠላምታ ጋር

አክሊሉ ተገኝ ማርቆ
Aklilu Tegegne Marku

**ግልባጭ**

- የቤንች ማጅ ጫካ ቡና አምራቾች ኃ/የተወሰነ ህ/ሥራ ዩንዬን

ሚዛን-አማን

ስለነበር ሁሉም አመራር ትኩረቱ በተፈጠረው ችግር ላይ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጦር ሜዳ ላይ መሄዳቸውን እየተመለከትን እኛ ስለዩንየኑ ብንጮህ ትክክል አይሆንም። ሀገር በከፍተኛ ችግር ውስጥ እያለች ለህብረት ስራ ንግድ ተብሎ ሌላ ችግር መፍጠር ተገቢ አይደለም። ምክንያቱም ንግድ የሚነገደው ሀገር ሰላም ስትሆን ነው ፤ ንግድ በህይወት የሚኖሩ ሰዎች ለመኖር የሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንጂ ጦርነት በሚካሄድበት ወቅት የሚደረግ አይደለም። የሰው ልጅ የሚሰራው የተሻለ ኑሮ ለመኖር በማሰብ ነው። የንግድ ውድድሩም በዚያው ልክ ነው። ሀገር በጦርነት ውስጥ ሆና የመንግሥት መዋቅር ለማህበራት አይደለም መደገፍ ችግራቸውን ለማየት እና ለመስማት የሚፈለግ አልነበረም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በ2013ዓ.ም በገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ወደ ቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች ዩኒየን ቢሮ ያቀናል። በዚህ ወቅት ዩኒየኑ ለሀገር እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ አድንቆ የቫት ተጠቃሚ ቢሆኑ ደግሞ ሀገርን የበለጠ በመጥቀም እንደሚችል ለዩኒየኑ ሥራ አስኪያጅ ይገልጻል። ሥራ እስኪያጁም እንደዜጋ የሚጠበቅባቸውን ለማድረግ ይስማማሉ።

የዩኒየኑ ሥራ አስኪያጅ በመንግሥት ሥራ በአመራርነት አገልግለው ስለነበር የቫት ተጠቃሚ ለመሆን መጀመሪያ ኦዲት መደረግ እንዳለባቸው ይረዳሉ። የገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ህብረት ስራ ዩኒየኑን ኦዲት ለማድረግ ጥያቄ አቀረበ። ዩኒየኑም የገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርንጫፍ ጥያቄን በቅንነት ተቀብሎ ኦዲት እንዲደረግ ፈቀደ።

ነገር ግን የጅማ ቅርንጫፍ ዩኒየኑ በ2000ዓ.ም አካባቢ የቫት ደረሰኝ አሳትሞ ነበር በሚል ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ 41 ሚሊዮን ብር መሰብሰብ እንዳለበት በምርመራ የኦዲት ግኝት ማግኘቱን አሳወቀ። በግኝቱ መሰረት የተገኘውን 41 ሚሊዮን ብር ህብረት ስራ ዩኒየኑ እንዲከፍል ጠየቀ። ሥራ አስኪያጁም እንዴት? የሚል ጥያቄ ማንሳታቸውን ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ገንዘቡን ካልከፈላችሁ በሚል የዩኒየኑን እና ሥራ አስኪያጁን የባንክ አካውንት ዘጋ።

ይህን ተከትሎ ሥራ አስኪያጁ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የተለያዩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የደረሰ ጥያቄ አቀረበ። በተለይም የገንዘብ ሚኒስቴር ኦዲት የተደረገው ልክ አለመሆኑን ገልጾ፤ ቅጣቱና ወለድ እንዲነሳ ወሰነ። ይሁን እንጂ ፍሬ ግብሩን ግን የማንሳት ስልጣን የሚኒስቴሮች ምክር ቤት መሆኑን ተነገራቸው። በዚህ ውሳኔ ለመጠቀም ጉዳዩን በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ በኩል ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ሶስተኛ ዙር ደብዳቤ በኢሜል መጻፋቸውን ያስረዳሉ። በተለያዩ ቢሮዎች ባደረግናቸው ማመልከቻዎች አሁን ላይ ዩኒየኑ 18 ሚሊዮን እንዲከፍል ተወስኖበታል።

ዩኒየኑ ለውጭ ገበያ በሚያቀርበው ቡና በዓመት ከ10 ሚሊዮን በላይ ዶላር ለሀገሪቱ ያስገኝ ነበር። አሁን ላይ ህብረት ስራ ዩኒየኑ ግብር አልከፈለም በሚል አካውንቱ በመዘጋቱ ከአርሶ አደር አልፎ ለሀገሪቱ የሚያስገኘው ዶላር ሙሉ በሙሉ ቆሟል። ይህንንም የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ካደረገው ኦዲት ማየት ይቻላል። በዩኒየኑ ላይ በሚደረገው ነገር እንደ ግለሰብ በጣም አዝናለሁ የሚሉት ሥራ አስኪያጁ፤ የእርሳቸው ትልቁ ሃሳብ በኮፕሬቲቭ ዘርፍ ደሃው ገበሬ አድጎ ማየትን እንደነበር ይገልጻሉ።

የገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አገኘሁት ባለው የምርመራ ኦዲት የስምንት ዓመት የቫት ግብር ክፈሉ ባላቸው ጊዜ የቤንች ማጂ የጫካ ቡና የገበሬዎች ዩኒየን ተቃውሞ አነሱ። የተቃውሞው መነሻም ዩኒየኑ የቫት ደረሰኝ ሳያሳትም እንዴት የቫት ግብር ይሰበሰባል? የሚል ነበር። አቤቱታ አቅራቢው ቀደም ባለው ጊዜ ገቢዎች ቢሮ መስራታቸውን አውስተው፤ የገቢ ደረሰኝ የሌለው ነጋዴ ካለ የገቢ ደረሰኝ አውጥቶ እንዲሰራ እንደሚደረግ ያስረዳሉ።

በህጉ መሰረት ዩኒየኖች ገቢ መሰብሰብ የሚችሉት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኝ

# በገቢ ግብር ውዝግብ ምክንያት ሊበተን ጫፍ ...

**ከ6ኛ ገፅ የዞረ**

የህብረት ስራ ኤጄንሲ በሚያሳትመው ደረሰኝ ነው:: ይህ ስልጣን ለህብረት ስራ ኤጀንሲው የተሰጠ ነው:: በአጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙ ዩኒኖች ገቢ የሚሰበሰበው የህብረት ስራ ኤጄንሲ በሚያሳትመው ደረሰኝ ብቻ ነው:: ገቢዎች ደግሞ የህብረት ስራ ኤጀንሲ በሚያሳትመው ደረሰኝ የምትሰበስቡ ከሆነ የሀገር ገቢ ይቀራል የሚል ቅሬታ አነሳ::

ይህ እውነት ነው:: አዋጅ ላይ ቢኖርም እንደ ባለሙያ በግሌ ኮፕሬቲቭ በኤጀንሲ የተደገፈ ሆኖ እንዲኖር አልፍልግም:: የተፈለገው ቫት እና ቅድመ ግብር እንድንሰበስብ ነው:: ምክንያቱም ዩኒኖች ከግብር ነጻ ናቸው:: እሱን መሰብሰብ ነበረብን እንጂ ግብር የምንከፍል ሰዎች አልነበርንም:: ምክንያቱም እኛ የገበሬዎች "ኤጀንት" ነን:: ነገር ግን ገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርጫፍ ጽህፈት ቤት "በህገወጥ ደረሰኝ ግብር ሰብስበህ ጥቅም ላይ አውለሀል የሚል ነው::" "ይህ ትክክል አይደለም" ሲሉ ይገልጻሉ::

ዩኒየኑ እንደ ኤጀንት ከአርሶ አደሩ ቡና ሰብስቦ ለማዕከላዊ ገበያ በማቅረብ በኢትዮጲያ ምርት ገበያ በኩል እንዲሸጥ ያደርጋል እንጂ በራሱ ገበያ አፈላልጎ ለገበያ አያቀርብም:: በመሆኑም ቡናው ከተሸጠ በኋላ ዩኒየኑ ከተሸጠው ቡና የኮሚሽኑን ብቻ ወስዶ ለአርሶ አደሮች ገንዘቡን ያከፋፍላል::

ዩኒየኑ 15 በመቶ የሚሆነውን ከአርሶ አደሮች የተሰበሰበን ቡና በሀገር ውስጥ ይሸጣል:: ነገር ግን ከዚህም ምንም ገንዘብ ተቀናሽ ሳይደረግ ለአርሶ አደሮቹ ገንብ ይከፈላል:: እኛም ያደረግነው ከቡና ሽያጭ ከሚገኘው ገንዘብ ምንም ሳንቆርጥ ለቡና አምራች አርሶ አደሮች ገንዘብ እንከፍላልን ያሉት አቶ ጌታሁን፤ ይህን ደግሞ ገቢዎችም እንደሚያውቁ አመላክተዋል::


ገንዘቡ ለአርሶ አደሮች መሰጠቱን የሚያውቀው ገቢዎች "ገንዘቡን ከአርሶ አደሮች መልሳችሁ ሰብስቡ" ሲል ለዩኒየኑ አሳወቀ:: ዩኒየኑም ለ21 ሺ አባል አርሶ አደር ያከፋፈሉትን ገንዘብ መልሶ መሰብሰብ እንደማይችል ገልጾ፤ ከዚህ በፊት ከተከናወነ ሽያጭ አሁን ላይ ከአርሶ አደሩ ግብር መጠየቅ በአካባቢው የሰላም ችግር ሊያስከትል እንደሚችል አሳወቀ:: የዞኑ አስተዳዳሪም ይህን እንደሚረዱ አስገነዘበ:: ነገር ግን ሰሚ አልተገኘም:: በመሆኑም የዞኑ አስተዳዳሪም ጭምር ስለጉዳዩ ከገቢ እና ጉምሩክ እስከ ገንዘብ ሚኒስቴር ድረስ ሄደው አቤት ማለታቸውን ይናገራሉ::

የገንዘብ ሚኒስቴር ቡናው የተሸጠው በሀገር ውስጥ ገበያ ወይም በውጭ መሆኑን አረጋግጣችሁ ግብሩን ቀሪ አድርጉ ብሎ ደብዳቤ ለገቢዎች ሚኒስቴር ጻፈ:: ነገር ግን የጅማ ገቢዎች ቅርንጫፍ እኛ የውጭ ገበያ የተሸጠው ላይ ሳይሆን በሀገር ውስጥ በሹጡት ቡና ላይ ነው ግብር የጠየቅነው የሚል ምላሽ ሰጠ:: ዩኒየኑ ሲሸጥ የነበረው ሀገር ውስጥና ውጭም ነበር:: ሀገር ውስጥ አልሸጥንም አላልንም የሚሉት አቶ ጌታሁን፤ ነገር ግን ቡናው ሲሸጥ ከገበሬዎች ላይ ለግብር ተቀናሽ አለማድረጋቸውን መግለጻቸውን ይናገራሉ::

ከዩኒየኑ ጋር ተያይዞ የነበረውን እውነታ ያውቁ የነበሩት የዞኑ አስተዳዳሪ የዩኒየኑ አባል የሆኑት አርሶ አደሮችን ከዚህ ቀደም በተደረገው የቡና ሽያጭ ከወሰዳችሁት ገንዘብ የተወሰነውን መልሳችሁ መክፍል አለባችሁ የሚል ትእዛዝ ለማስተላለፍ ሞከሩ:: ነገር ግን ዩኒየኑ ከ21 ሺህ በላይ ገበሬ ላይ እንዴት አድርጎ ነው ገንዘብ መሰብሰብ የሚችለው? የሚለውን መፍትሔ ማስቀመጥ አልተቻለም:: በመሆኑም እስካሁን የተጠየቅነውን ገንዘብ መክፈል አልቻልንም:: በገቢዎች ሚኒስቴር ጅማ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት "ዩኒየናችሁን የምትፈልጉ ከሆነ 18 ሚሊዮኑን ብር ክፍሉ" እያለ ነው::

በፌዴራል ህብረት ስራ ኮሚሽን ጭምር ችግሩን ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት በደብዳቤ ማሳወቃቸውን የሚናገሩት አቶ ጌታሁን፤ ነገር ግን እስካሁን ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት መልስ ስላልተገኘ እስከሁን ድረስ የህብረት ስራ ዩኒየኑ እና የሥራ አስኪያጁ የባንክ ሂሳብ መዘጋቱን ጠቁመዋል::

ጥሩ የሚሰራ ዩኒየን ስለነበር የተለያዩ ተሸከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ መኪና አስገብቶ ነበር:: በዩኒየኑ ስር የሚተዳደሩ 21 የሚሆኑ ኢንዱስትሪዎች ያሉ ሲሆን፤ እነዚህ ማሽነሪዎች ወደሀገር የገቡት ከቀረጥ ነጻ በሆነ መንገድ ነው::ከጅምሩ ጀምሮ ዩኒየኑ መንግሥትን የበደለው ነገር የለም:: በዩኒየኑ ውስጥ


በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. ታ/ክ/ቀ/5/413
ቀን / Date 8/9/2014

ለገቢዎች ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

የቤንቺ ማጂ የጫካ ቡና አምራች ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን ከአባላቱ ተሰብስቦ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ወደ ውጭ በተላከ ቡና ላይ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ፍሬ ግብር፣ ወለድና ቅጣቱን ጨምሮ ብር 25,790,450.90 እንዲሁም ቅድመ ግብር ፍሬ ግብር፣ ወለድና ቅጣት ጨምሮ በድምሩ ብር 5,963,199.19 እንዲከፍል የተጠየቀ መሆኑን፣ በዚሁ የታክስ ጫና ምክንያት የባንክ ሂሳቡ በመታገዱ ምክንያት ሥራ ለማቆም የተገደደ በመሆኑ ዩኒየኑ ለአገር የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪ ግኝት የተቋረጠ መሆኑን፣ በአካባቢው ማህበረሰብ እና በግለሰብ አባላት ዘንድ ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ የፈጠረ መሆኑን በመግለፅ ጉዳዩ በመ/ቤታችን በኩል ታይቶ እልባት እንዲሰጠው የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር አጠ34/1610 በተፃፈ ደብዳቤ የጠየቀውን ይመለከታል።

በዚህም መሠረት፡-

1. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 280/2002 አንቀጽ 7(2) መሠረት የቡና ወጪ ንግድ ግብይት በዜሮ በመቶ (Zero rated transaction) የማስከፈያ ልክ የሚስተናገድ በመሆኑ የቡና ምርቱ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ወደ ውጪ የተላከ መሆኑ ተረጋግጦ የታክሱ ክፍያ ቀሪ እንዲደረግ፣ እንዲሁም
2. ዩኒየኑ በተፈጠረ የሕግ ብዥታ ምክንያት የቅድመ ግብሩን ክፍያ ሊሰበስብ ያልቻለ መሆኑን ማረጋገጥ የተቻለ በመሆኑ ለመ/ቤታችን በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 13(3) እንዲሁም በፌዴራል ታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 407/2009 አንቀጽ 7 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት እንዲከፍል የተጠየቀው የግብር ዕዳ (ወለዱና ቅጣቱን) ጨምሮ በምህረት ቀሪ እንዲደረግ፣

የተወሰነ መሆኑን እየገለፅን በዚሁ መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፣
ለኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
አዲስ አበባ

LetterH/E

ስልክ 251-11-155 24 00,22 66 98
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFED

ታቅፈው ያሉ አርሶ አደሮች ህይወታቸውን ለውጠዋል:: ቡና ወደ ውጭ ሀገር በመላክ ለሀገራችን ከ10 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት ችሏል:: በዚህም ዩኒየኑ "በካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ" ተሸላሚ መሆን የቻለ ነው::

በገቢዎች ሚኒስቴርም እንደ ዩኒየን አመራር ብዙ ተቃውሞ የለኝም:: ነገር ግን ዩኒየኑ ስራ እንዳይሰራ በመደረጉ የበርካታ የህብረተሰብ ክፍሎችን ኢኮኖሚ የጎዳ ከመሆኑም ባሻገር የስራ ተነሳሽነትንም እያዳከመ ነው:: አሁንም የጅማ ቅርንጫፍ የባንክ ሂሳባቸውን ዘግቶ በመያዙ መጋዝን ላይ ያለውን ቡና መሸጥ አለመቻላቸውን ጠቅሰው፤ አርሶ አደሩም እየመጣ ገንዘባችንን ስጡን እያለ እየጠየቀ መሆኑን ጠቁመዋል::

በዚህም የዞኑ አስተዳደር ጭምር የጅማ ቅርንጫፍ ገቢዎችን እስከማነጋገር መድረሱን ይገልጻሉ:: ነገር ግን የተሰጠው ምላሽ የተጠየቀውን ግብር 25 በመቶ ከፍሎ ክስ መመስረት እንደሚችል እና ክስ እስከሚመሰረት ድረስ የባንክ ቼክ ወይም ንብረት በማስያዝ ስራ ይቀጥል የሚል ምላሻ ነው::

ዩኒየኑ መጋዘን ላይ የ29 ሚሊዮን ብር አለው:: ነገር ግን ቡና ለመሸጥ ሲታሰብ ሥራ የአስኪያጅ ሆነ የዩኒየኑ አካውንት ዝግ ነው:: በቡና ጉዳይ ገበያ የመጣው ሁሉ ተጠያቂ እሆናለሁ በሚል ፈርቶ ይሸሻል:: አሁን ላይ ክፈሉ የተባለውን 18 ሚሊዮን ብር የዩኒየኑን ተሽከርካሪዎች እና የቡና ኢንዱስትሪዎች በባንክ እንደ ዋስትና በማስያዝ ለመክፈል እየተሞከረ ነው::

ዩኒየኑ ጥፋት ባልሰራበት አካውንቱ ታግዶ ለኪሰራ እና ለብተና እየተዳረገ ነው:: ቡና ሸጦ በስሩ ለሚገኙ 21 ሺህ አርሶ አደሮች አከፋፈለ ተከፋፈለ እንጂ ለሌላ ዓላማ አልዋለም:: ብሩን እንሰብስብ ቢባል እንኳን 21 ሺህ አርሶ አደር ላይ እየዞሩ ይህን ያህል ብር አምጣ ማለት ከባድ ነው::

እንደ አቶ ጌታሁን ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም ግብር ለመሰብሰብ በመፈለግ ለደብብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ደብዳቤ ጽፈዋል:: ነገር ግን ለደቡብ ብሔር ብሔረረሰቦችና ህዝቦች ክልል ህብረት ስራ ኤጀንሲ መሰብሰብ አትችሉም ብሎ በአዋጅ ጠቅሶ እንዳስቆማቸው እና በዚያ መሰረት ግብር ሳይሰበስቡ መቅረታቸውን ያስረዳሉ::

አሁን ላይ ዩኒየኑ ብቻ ሳይሆን ብድር አቅራቢ የነበሩ ባንኮች ጭምር እየተጎዱ ነው:: የባንክ ወለድ ብቻ 50 ሚሊዮን ብር ደርሷል:: ሶስት ዓመት ሙሉ ቡና መሰብሰብ አልተቻለም:: 21 የሚደርሱ ኢንዱስትሪዎች ስራ አቁመዋል:: ከ280 ሰራተኞች መካከል አሁን ላይ የቀሩት 31 የሚሆኑት ናቸው:: እነዚህም ቢሆን ደመወዝ ተከፋይ አይደሉም::

### ከሰነዶች የተገኙ ማስረጃዎች

ሰነድ አንድ፡- ለሚመለከተው ሁሉ በሚል በደብዳቤ ቁጥር ግሕቢ/አ14/1/538/07 በቀን 16/03/07 በተጻፈ ደብዳቤ እንደተመላከተው፤ የቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን በፌዴራል ኅብረት ሥራ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 እና በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ምክር ቤት በወጣው የኅብረት ሥራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 111/1999 መሠረት ተቋቁሞ የምዝገባ ህጋዊ ሰውነት የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቶት ሲሰራ ቆይቷል::

ይሁንና ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በግዥ፣ በሽያጭና በጨረታ ላይ ለመሳተፍ ውድድር በሚያካሂድበት ወቅት አለአግባብ የንግድ ፈቃድ የቫት ተመዝጋቢ ስለመሆኑ ማስረጃ እንዲያቀርቡና ቲ.ኦ.ተ እንዲከፍሉ እየተገደዱ መሆኑን ገልጾ፤ በቁጥር 1167/ሕ-6ደ/2007 በቀን 2/03/2007 በተፃፈ ማመልከቻ ተጨማሪ የንግድ ፈቃድ ሳያስፈልግና ተ.ኦ.ተ እንዳይቆረጥባቸው የድጋፍ ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት የግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ ጠይቀዋል::

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት የግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ ለተጠየቀው ጥያቄ ለሚመለከተው ሁሉ በሚል በቁጥር ግሕቢ/አ14/1/538/07 በቀን 16/03/07 በተጻፈ ደብዳቤ እንደተመላከተው ፤የቤንች ማጂ የጫካ ቡና አምራች ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን በፌዴራል ኅብረት ሥራ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 እና በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ምክር ቤት በወጣው የኅብረት ሥራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 111/1999 መሠረት ተቋቁሞ የምዝገባ ህጋዊ ሰውነት የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቶት ሲሰራ መቆየቱን ጠቅሷል::

በዚሁ መሠረት የኅብረት ሥራ ዩኒየኑ በአዋጅ ቁጥር 111/1999 አንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ 7 ላይ በህጋዊ መንገድ የተመዘገበ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ተጨማሪ የንግድ ፈቃድ ሳያስፈልገው በማንኛውም የንግድ ሥራ ተግባራት ላይ መሰማራት እንደሚችል አመልክቷል:: በተጨማሪም በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 41 ንኡስ አንቀጽ አንድ በተራ ፊደል "ረ" ላይ በመንግሥት የሚከናወኑ የአገልግሎት የኮንስትራክሽን የማምረት የግብይት እና ሌሎችም ጨረታዎችን የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለኅብረት ሥራ ማህበራት በሚያሟሉት ደረጃ ቅድሚያ ሊሰጥ ይችላል በሚል ልዩ መብት ተሰጥቶታል።

እንዲሁም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግሥት የታክስ አስተዳደር ባለስልጣን ታህሳስ 2000 ዓ.ም ከተካፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ሥርዓት የአፈጻጸም መመሪያ የተሻሻለው አንቀጽ 2.4.6 ላይ ከተካፋይ ሂሳቦች ላይ ግብር ተቀናሽ የማይደረግባቸው የገቢ ዓይነቶች አካላትና ግብይቶች በሚለው አንቀጽ ሥር በገጽ 16 በተራ ቁጥር ስምንት መንግሥታዊ ያልሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች ማለትም ብዙኃን ማህበራት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወዘተ ከፍትህ ሚ/ር እና ከሚመለከተው አካል የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሲያቀርቡ ላከናወኑት የዕቃ፣ የንብረት ሽያጭ ለሰጡት አገልግሎት ክፍያ ሲፈጸምላቸው ከተካፋይ ሂሳብ ተቀናሽ አይደረግባቸውም በሚል መደንገጉን ተመላክቷል::

ሰነድ ሁለት፡-የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/413 በቀን 8/9/2014 ለገቢዎች ሚኒስቴር በተጻፈ ደብዳቤ እንደተመላከተው፤ የቤንቺ ማጂ የጫካ ቡና አምራች ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን ከአባላቱ ተሰብስቦ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ወደ ውጭ በተላከ ቡና ላይ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ፍሬ ግብር፣ ወለድና ቅጣቱን ጨምሮ ብር 25 ሚሊዮን 790ሺህ 450 ነጥብ ዘጠኝ እንዲሁም ቅደመ ግብር፣ ፍሬ ግብር፣ ወለድና ቅጣት ጨምሮ በድምሩ ብር 5 ሚሊዮን 963 ሺህ 199 ነጥብ 19 እንዲከፍል ተጠይቋል::

በዚሁ የታክስ ጫና ምክንያት የባንክ ሂሳቡ በመታገዱ ምክንያት ሥራ ለማቆም ተገዷል:: በመሆኑም ህብረት ስራ ዩኒየኑ ለሀገር የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪ ግኝት የተቋረጠ በመሆኑ፣ በግለሰብ አባላት ዘንድ ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ የፈጠረ መሆኑን በመግለፅ ጉዳዩ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ታይቶ እልባት እንዲሰጠው የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር አጠ34/1610 በተፃፈ ደብዳቤ መጠየቁን ግልጾ በዚህም መሠረት፡-

አንደኛ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 280/2002 አንቀጽ 7(2) መሠረት የቡና ወጪ ንግድ ግብይት በዜሮ በመቶ (Zero rated transaction) የማስከፈያ ልክ የሚስተናገድ በመሆነ የቡና ምርቱ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ወደ ውጪ የተላከ መሆኑ ተረጋግጦ የታክስ ክፍያ ቀሪ እንዲደረግ፤ እንዲሁም ዩኒየኑ በተፈጠረ የሕግ ብዥታ ምክንያት የቅድመ ግብሩን ክፍያ ሊሰበስብ ያልቻለ መሆኑን ማረጋገጥ የተቻለ በመሆኑ ለገንዘብ ሚኒስቴር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 19(3) እንዲሁም በፌዴራል ታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 407/2009 አንቀጽ 7 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት እንዲከፍል የተጠየቀው የግብር ዕዳ (ወለዱና ቅጣቱን ጨምሮ በምህረት ቀሪ እንዲደረግ፤ የተወሰነ መሆኑን እየገለፅን በዚሁ መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ እናሳስባለን የሚል ነው::

ውድ አንባቢያን በቀጣይ ከገቢዎች ሚኒስቴር የሚሰጠውን መልስ፤ አዋጅ እና መመሪያዎች ምን ይላሉ የሚለውን ይዘን የምናቀርብ ይሆናል::

# ነፃ ሃሳብ

# “የትርክት ዕዳና በረከት” መጽሐፍ...

ከገጽ 5 የዞረ

ችግሩን በዚህ ልክ መረዳት ከተቻለ፣ ለዚህ ችግር መፍትሔ ማስቀመጡ ይበጃልና፣ ታሪኩ ያልተጻፈ እንጂ ታሪክ የሌለው ማኅበረሰብ ባለመኖሩ የጎደለውን እየሞሉ ታሪካችን ሁሉንም አቃፊ ወይም አካታች እንዲሆን መሥራት፣ ጥፋቱም ሆነ ልማቱ የጋራችን መሆኑን ማመን፣ የተፈጸመውን ጥፋት በይቅርታ ማለፍ ከችግሩ ልቆ መሻገሪያ፣ ዕዳውንም ወደ በረከት መቀየሪያ አቅም መሆኑን ያስገነዝባል።

ከዚህ አኳያ፣ ታሪክ ዛሬ ላይ ሆኖ ስለትናንት የሚተርክ መሆኑ አጠያያቂ ባይሆንም፤ በዛሬ ድልድይነት የትናንትን መልካም ዕሴት ወደ ነገ በማሸጋገር ወይም ትናንትን ከነገ በማገናኘት ትውልድን የሚያኮራውንና ሀገራችንን የሚያስከብረውን ማስቀጠል የሚገባ መሆኑ መታወቅ አለበት። እንዲህ ያለው ተግባር እውን የሚሆነው ደግሞ ከተጻፈው ታሪካችን የጎደለው እየተሞላ፤ ያልተስተካከለውም እየተቃና አካታች ሲሆን ነው። ይህ እውን የሚሆነው ደግሞ ታሪካችን በሙያው አንቱ በተባሉ የታሪክ ተመራማሪዎች በጥልቀት ሲጠና ነው።

“የትርክት ዕዳና በረከት” ጸሐፊ እንደገለጹት፤ ታሪካችን በምርምር እየዳበረ እንዲሄድ ከማድረግ ባሻገር፤ በየቦታው በቀደምት ኢትዮጵያውያን የተፈጸሙትን ታሪኮች እና ሥልጣኔዎች “የእኛ ናቸው” ብለን ልንቀበላቸው ይገባል። በልዩ ልዩ ቦታዎች የተፈጸሙ ታሪኮችን “የእኛ ናቸው” ብሎ መቀበል ሲባልም፤ በዘመናት ሂደት በተጻፈው ታሪካችን መካከል ስሕተት ተካትቶ ቢሆን እንኳ ስሕተቱን እያስተካከሉ፣ የጎደለውን እየሞሉ መሄድ እንጂ፤ እኛ የጉዳዩ አካልም፣ ባለቤትም አይደለንም ማለት ተገቢ አይደለም። ትርክትን የሚያቃናው እና ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆን የሚያደርገውም እንዲህ ያለው ተግባር ነው።

ጸሐፊው በመጽሐፉ ደጋግሞ እንደገለጸው፤ የታሪክ መነጽር የሚቀየረው ሰዎች ታሪክን ሊጠቀሙበት የፈለጉበት መንገድ ወይም እይታ ሲቀየር ነው። በዘመን ሂደት የተፈጸመን የሀገር ታሪክ፣ ከሀገር ይልቅ ግላዊ ጥቅምን በማስቀደም የእኛ አይደለም ብሎ መካድም ሆነ፤ የእነርሱ እና የእኛ ብሎ መከፋፈል የትርክታችን ዕዳ ሆኗል። በመሆኑም ይህን ዕዳ ወደ በረከት ለመቀየር ከግል ጥቅም ይልቅ ሀገርን ማስቀደም፤ በሀገራችን የተፈጸመውን ጥፋትም ይሁን ልማት ሁሉ የእኛ ነው ብሎ መቀበል ይገባል። ሀገራችን ከገጠማት ዕዳ የምትወጣበት መሰላልም ይሄው ነው።

ከዚህ በተቃራኒው ተጉዘን፣ በሀገራችን የተፈጸመውን ታሪክም ሆነ ሥልጣኔ የእኛ ብለን አለመቀበላችን እና እነርሱን እንጂ እኛን አይወክለንም ማለታችን ብዙ ታሪክ በተፈጸመበት ሀገር እየኖርን ታሪክ እንዳንማር እንቅፋት ፈጥሮብናል። ለምሳሌ፣ በዩኒቨርሲቲዎቻችን የታሪክ ትምህርት እንዲሰጥ ሲደረግ፣ የእነ እገሌ እንጂ የእኛ ታሪክ አይደለም የሚሉ፤ ከሚያቀራርቡ ይልቅ የሚያለያዩ ነጥቦችን መምዘዙ ባሰ።ይሄን መሰሉ እንከን እየመዘዙ መነታረክን መፍጠር ደግሞ ትርፉ እዳ ስለመሆኑም አመላክቷል።

ታሪክ መማሪያ እንጂ መማረሪያ እና ሻምላ መማዘዣ እንዳይሆን በመስጋት ትምህርቱ እንዳይሰጥ ሆኗል። እንዲህ ያለው ተግባር ደግሞ ትርክት ያስከተለው ዕዳ ስለሆነ፤ መነታረኩን ወደ መተቃቀፍ፣ ልዩነቱን ወደ አንድነት፣ ነጠላ የሆነውን ትርክት ወደ አካታች ትርክት ለመለወጥ የታሪክ ጥናትን በማጎልበት የጎደለውን መሙላት፣ የጠፋውን ፈልጎ ማግኘት፣ የተጣመመውን ማቃናት፣ ያልተካተተውን ማካተት ያስፈልጋል።

በዚህ ረገድ የዛሬ አመለካከት በተቀየረ ቁጥር የታሪክ ትርክት መቀየሩ የታመነ ቢሆንም፤ ታሪክን የማቃናት ሂደቱ በወጉ ካልተያዘ መልካም የነበረው ወደ መጥፎ፣ መጥፎ የነበረውም ወደ በለጠ መጥፎ የመቀየር ዕድል ስለሚኖረው በትኩረት ሊከወን የሚገባው ጉዳይ ነው። ይሄን በማድረግም ነው መጥፎው አመለካከት ወደ መልካም እንዲቀየር ትርክትን መቀየር የሚገባውም፤ የሚያስፈልገውም።

ጸሐፊው አያይዞ ሲገልጽም፤ ትርክትን መቀየር ማለት ያልተፈጸመውን የተፈጸመ አድርጎ፣ የተፈጸመውን ደግሞ እንዳልተፈጸመ ቆጥሮ ማለፍ አይደለም። ይልቁንም የጎደለውን እየሞሉ የእኔ ታሪክ አልተካተተም የሚል ስሜት እንዳይፈጥር ሁሉን አቀፍ ወይም አካታች በማድረግ ውስጥ የሚከናወን ነው።

ምናልባት፣ የተጣመመ ትርክት ያስከተለውን ዕዳ ወደ በረከት ለመለወጥ የሚያስችል ምን ጉዳይ አለ የሚል ጥያቄ የሚያነሳ ቢኖር፤ ጸሐፊው፣ “የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ ሕመም ሞልቷቸዋል። የታሪክ አጻጻፋችን ግን የአካታችነትና የብያኔ ችግር አለበት። የእኛ ዘመን የታሪክ ሊቃውንት ዋናው ሥራም የማቃናትና የማካተት ተግባር ነው።

ለዚህ የሚሆኑ መረጃዎችና ማስረጃዎች ደግሞ ሞልተዋል፤” (ገጽ 81)፣ ሲል አመላክቷል። በመሆኑም የሚጻፈው ታሪክ፣ በየአጋጣሚው የኢትዮጵያ ተብለው የሚቀርቡ ዝግጅቶች፣ ትዕይንቶች እና ሌሎችም ነገሮች ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ማካተት ሲችሉ፤ ይህማ የእነ እገሌ እንጂ የእኔ ባለመሆኑ አይወክለኝም የሚሉ ወገኖች እየቀነሱ፤ የእኛ ነው የሚሉ ወገኖች እየበዙ ይሄዳሉ።

> **ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ለማምጣት ኅብረ ብሔራዊነትን ከአንድነት ጋር አጣምሮ የያዘ፣ ትናንትን አግባብቶ ለነገ የሚያሻግር ስትራቴጂካዊ ትርክት ይፈልጋል**

እንዲህ ያለውን ችግር ለማስወገድ መፍትሔ በማለት ጸሐፊው ከገለጸው መካከል፤ “ሁነኛ መፍትሔው የታሪክ ጥናትን በማበረታታት ሁሉንም ዓይነት ማኅበረሰብና ሁሉንም ዓይነት የማኅበረሰብ የታሪክ መልኮች እንዲዳስስ ማድረግ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ የሚባል አለን። ግን የተሟላ አይደለም። መቼም ደግሞ አይሟላም። እየተሟላ መሄድ ግን ይችላል። ለዚህ ደግሞ የታሪክ ጥናት መስክን ማበረታታት ነው፤” (ገጽ 103)በማለት ያሰፈረው ሃሳብ ይገኝበታል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ “ትርክቶች የትናንት ታሪኮችን እንደ እርሾ በመጠቀም ዛሬ ላይ ለምንፈልገው አሉታዊም ይሁን አዎንታዊ ፍላጎቶቻችን የምንጠቀምባቸው፣ ፍላጎቶችን የምናሰባስብባቸው መሣሪያዎች ናቸው። ትርክት ተቀባይነት የሚኖረው ስለማኅበረሰቡ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ግልጽ በሆነ የጊዜና የድርጊት ፍሰት ሲቀርብ፣ ድርጊቱ ደግሞ ትርጉም ባለው ሁኔታ መቀመጥ ሲችል ነው።

ትርክቶችን በአግባቡ መረዳት በዘመኑ ውስጥ የተስተናገዱትንና የነበሩትን በርካታ የተበታተኑ ክስተቶች በወቅትና በቦታ በማደራጀት እና በማቀናጀት በማኅበረሰቡ ዙሪያ ስለነበረው ሁኔታ ማወቅ፣ መረዳትና ማስተዋል እንዲሁም ማኅበራዊ ማንነቶቻቸውን (ዕሳቤያቸውን) በመገንዘብ ዛሬ ላይ የሚበጀንን የአኗኗር ሥርዓት ለመመሥረት ያስችላል፤” (ገጽ 108)፣ ስልም ትርክቶችን ከእዳነት ወደ በረከትነት የመቀየርን አካሄድ አስረድቷል።

ገንቢም ሆነ ጎጂ ትርክት ዓላማ ያለው መሆኑ፣ ታስቦበት ወይም በዘፈቀደ መዘጋጀቱ በጸሐፊው ተጠቅሷል። የኢትዮጵያ የሆነውን ሁሉ የአንድ ወገን አስመስሎ ማቅረብም ሆነ፤ የሌሎች እኔን አይመለከተኝም የሚለው አስተሳሰብ በአንድ በኩል ያለመካተት ችግር ያስከተለው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ፖለቲካውን በዘር ተደራጅተው የሚመሩ አካላት የሚያደርጉት ቅስቀሳ ውጤት መሆኑን፡-

“ የቋንቋ መዋረሶች እንደ ጸጋ ሳይሆን እንደ መወረርና ማንነትን እንደ ማጣት ተደርገው ይወሰዳሉ። በዚህ ምክንያት ጥያቄ እያነሡ መቆራቆሱ ዛሬም እንደ አዲስ ቀጥሏል። ይህ ደግሞ የብሔር ፖለቲካው ያዋለደው ዕሳቤ መሆኑን የታሪክና የፖለቲካ ሊቃውንት ይናገራሉ። ዛሬ ላይ በሀገራችን ቋንቋ ዳቦ ሆኖ ነፍስ ሲታደግ፤ በአንጻሩም ቋንቋ የጦር መሣሪያ እያስታጠቀና እያጋደለ ያለበት ጊዜ ላይ ደርሰናል ”

“ ቋንቋ በሁለት ጽንፍ ተቃርኖዎ እንዲገለጥ በማድረግ ሁነት ውስጥ መድረሳችን ደግሞ የፖለቲካችን የብስለት ችግር እንጂ የቋንቋዎች ችግር አይደለም። ምክንያቱም ቋንቋ በተለያዩ ምክንያቶች ሊስፋፉም ላይስፋፉም ይችላል። በደረስንበት ዘመን የተስፋፋውን መቀነስ ያልተስፋፋውን ደግሞ ጨርሶ መርሳት መፍትሔ አይደለም። ቋንቋዎች ሁሉ በቻሉት መጠን እንዲያድጉና እንዲከበሩ ማድረግ፤ በራሳቸው በቋንቋዎች ውድድርና ትስስር መርሕ እንዲመሩ መተው፤ እና ብዝኃነትን የሚያከብር ፖሊሲ መከተል ዘለቄታዊ መፍትሔ ሊሆን ይችላል” (ገጽ 86)፣ በማለት ችግሩን እስከ መፍትሄው ለማስቀመጥ ሞክሯል።

ከዚህ ገለጻ የምንረዳው፤የመጀመሪያው ነጥብ፣ የቋንቋ መዋረስን እንደ ጸጋ ሳይሆን እንደ መወረር ማየት ሀገራችንን እና ሕዝቦቿን ለችግር የዳረጋቸው መሆኑን ነው። ሌላው ነጥብ፣ የቋንቋ ልዩነት እንደ በረከት መታየት ሲገባው፤ ቋንቋን ወፍራም እንጀራ ለመብላት መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙ አካላት ከኋላ ሆነው ብዙኃኑን እየገፉ ጦር እንዲያማዝዝ ማድረጋቸው ነው። እንዲህ ያለው ዕሳቤ ደግሞ የብሔር ፖለቲካው ያዋለደው መሆኑን ጸሐፊው ገልጿል።

ሀገራችን እንዲህ ካለው የመጠፋፋት አዙሪት ውስጥ እንድትገባ ገፍቶ ያደረሳት የፖለቲካው የብስለት ችግር እንጂ የቋንቋዎች ችግር አለመሆኑንም ጸሐፊው አስገንዝቧል። ፖለቲካው ያስከተለው ችግር በዚህ ሳይወሰን ታሪክን አሽከር አድርጎ ያዘዘውን ሁሉ እንዲፈጽምለት ማስገደዱን “በእኛ ሀገር አሁን ታሪክ የፖለቲካ አሽከር ሆኗል። መማሪያ ሳይሆን መማረሪያ ሆኗል” ሲል ከገለጸው በኋላ፤ “ይህ ትውልድ ነቅቶ ታሪክን ትጥቅ በማስፈታት ሲቪል ማድረግ አለበት” (ገጽ 117)፣ በማለትም መፍትሔ ያለውን ሃሳብ ለትውልዱ አቀብሏል።

ሌላው በጸሐፊው መፍትሔ ተብሎ የተጠቀሰው ነጥብ፣ “ግልጽነት የጎደለውን አደናጋሪ ትርክት ለመፍጠር ከመቻኮል ይልቅ በዘመናዊነት የዲዛይንና የነባራዊነት አረዳድ ክፍተት ካለ በንግግርና በሞያዊ ሂስ ማስተካከል እንጂ፤ ለመነታረክና ለግጭት ማዋል ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፤” (ገጽ 99)፣ የሚለው ነው። ታዲያ እንዲህ ያለውን ምክር ተግባራዊ የሚያደርገው ቢገኝ ሀገራችን ከገባችበት ችግር የምትላቀቅ መሆኗ የታመነ ነው።

ታሪክን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያውያን የሆነውን ሁሉ፣ “የእኛና የእነርሱ በሚል ታሪክ ተሸብበን፣ አትድረስብኝ አልደርስብህም፣ አትይብኝ አላይብህም፣ ያንተ እንደ ታሪክ ይቆጠራል አይቆጠርም፣ በሚል ትርክት ታሪኮችን ከፍና ዝቅ ማድረግ ብዝኃነትን አለማክበርና ዋልታ ረገጥ ዕሳቤ የትናንት እስረኞች አድርጎናል፤” (ገጽ 144) ይላል ጸሐፊው።

“ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ለማምጣት ኅብረ ብሔራዊነትን ከአንድነት ጋር አጣምሮ የያዘ፣ ትናንትን አግባብቶ ለነገ የሚያሻግር ስትራቴጂካዊ ትርክት ይፈልጋል። ... ዓላማው ለትናንት፣ ለዛሬና ለነገ ወሳኝ የሆነ ትርጉም መስጠት ነው፤” (ገጽ 145-146)፣ በማለትም ለችግሩ መፍትሔ ያለውን አስቀምጧል። ትርክትን ኅብረ ብሔራዊ ማድረግ የሚቻለው ደግሞ አንዳችን ለሌላችን በመኖር ውስጥ መሆኑን ጸሐፊው ደጋግሞ በመጽሐፉ ውስጥ ገልጾታል።

ከትርክት በረከት ለመሳተፍ ወይም ትርክትን በኢትዮጵያውያን ሁሉ ቅቡል ለማድረግ ከሚያግዙ ተግባራት አንዱ በየአካባቢው ለሚገኙ ሥልጣኔዎች እና በየቦታው በኢትዮጵያውያን ለተፈጸሙ ታሪኮች ዕውቅና በመስጠት በአንድ አካባቢ የሚገኙ ሥልጣኔዎች የኢትዮጵያውያን ሁሉ መሆናቸውን መቀበል ዋነኛው መፍትሔ መሆኑንም አስገንዝቧል።

ጸሐፊው፣ የወል ትርክት ለመፍጠር በተቃርኖ ቁልፍ የተከረቸመውን መክፈት የሚቻልበትን መፍትሔ የጠቆመበት ሃሳብም፤ “ትንሣኤ ኢትዮጵያን ለማረጋገጥ ከቅንነት ባሻገር ከሕጸጽ የራቀ፣ የኢትዮጵያንን ኅብረ ብሔራዊ ሥልጣኔ የተገነዘበ እና የሕዝቦችን ተጨባጭ ፍላጎት ያማከለ የመበልጸግ ትርክትና አስተሳሰብ ያስፈልጋል፤” (ገጽ 516፣ 522)፣ የሚል ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በየዘመናቱ ሥልጣን ላይ በወጡ መሪዎች ከምዕራባውያንም፣ ከምሥራቃውያንም የተቃረሙ ርእዮተ ዓለሞች ቤተ ሙከራ ስትደረግ ኖራለች። እንዲህ ማድረጉ ከጥቅሙ ጉዳቱ በማመዘኑ፤ ብሎም የእኛ እና የእነርሱ እየተባባልን ለመቧደን ምክንያት በመፈጠሩ ወደ ራሳችን ማየት እና አካባቢያችንን ማማተር እንደሚገባን ጸሐፊው ይገልጻል።

ለዘመናት የየባህሉና የየቋንቋ ተናጋሪው ልሂቃን ሲጠቀምበት፣ ችግር ሲፈታበት፣ የተለያዩትን አንድ ሲያደርግበት፣ ለተተኪው ትውልድ ሲያስተላልፈው ወደ ኖረው የኢትዮጵያውያን ሁሉ ወደ ሆነው የልቡና ውቅር መመለስ እንደሚገባ መጽሐፉን ስናነብ የምንረዳው ሀቅ ነው።

አሁንም እንደ ገና ወደ ሌላ ሀገር ዕሳቤ ማማተር ሀገራችንን ለሌላ ዙር ቤተ ሙከራ መዳረግ መሆኑን፤ ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት “የትርክት ዕዳ እና በረከት” በሚለው መጽሐፉ ደጋግሞ ያስገነዘበው እውነት ነው። ሀገራችንን በየጊዜው እንደ አዲስ ጀማሪ ከማድረግ ይልቅስ ሀገር በቀል የሆነውን ዕሴታችንን ተጠቅመን፣ ዘመን ተሻጋሪ ተግባር ማከናወን እንደሚገባ አስገንዝቧል።

“ሀገራችንን ከቤተ ሙከራነት ለማውጣት ዋናው መፍትሔ ያለፈውን በትክክል መዝኖ ችግሩን እያስተካከሉ መሔድ ነው፤” (ገጽ 554)፣ በማለት ነው። እኔ ይሄን ያህል በወፍ በረር ካነበብኩት ካልኳችሁ፤ ቀሪውን እና እልፍ የምታተርፉበትን ሃሳብ ከመጽሐፉ እንድታገኙት ለንባብ በመጋበዝ ነው። ቸር ይግጠመን፤ ሰላም!!!

# የተጠናከረ ሥራን የሚጠይቀው ዋጋን የማረጋጋት ጥረት

**ሰሚራ በርሀ**





መንግሥት ለሀገሪቱ ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎችን ይዞ የመጣ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በቅርቡ ወደ ሙሉ ትግበራ ማስገባቱ ይታወቃል:: ማሻሻያውን ተከትሎም ብሄራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር ስርአት ማሻሻያ አውጥቷል:: የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር ስርአት ማሻሻያም በውጭ ምንዛሬ ግብይት ላይ የነበረውን ስር የሰደደ ችግር ለመፍታት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ታምኖበታል:: በማሻሻያው መሰረት የውጭ ምንዛሬ ከብሄራዊ ባንክ እጅ ወጥቶ በገበያ የሚመራበት ሁኔታ ተፈጥሯል::

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው እና እሱን ተከትሎ የወጣው የውጭ ምንዛሬ ግብይት አስተዳደር ስርአት ማሻሻያ ትልቅ የሚባሉ ውሳኔዎች መሆናቸውን የኢኮኖሚ ባለሙያዎችም አስታውቀዋል፤ ባለሙያዎቹ ትግበራው የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ስርዓት በጠበቀ መልኩ በጥንቃቄ መመራት እንደሚገባውም አስገንዝበዋል:: መንግሥትም የማሻሻያውን ትግበራ ተከትሎ የመልካም አስተዳደር ችግሮች፣ ህገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ በማመን ችግሮቹን ለመፍታት የበኩሉን እንደሚሰራ ባረጋገጠው መሰረት እየሰራ ነው::

ማሻሻያው ወደ ትግበራ እንደገባ ህገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎች መታየት ጀምረዋል:: የዋጋ ጭማሪ፣ ምርት መደበቅና የመሳሰሉት በስፋት ታይተዋል:: ምንም ኢኮኖሚያዊ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ሀገር ውስጥ በሚመረቱ ምርቶች ላይ ሳይቀር የዋጋ ጨማሪ ተከስቶ ህብረተሰቡን እየጎዳ ይገኛል::

ያነጋገርናቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችም ይህንኑ አረጋግጠውልናል:: ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ያገኘነው መረጃም ይህንኑ አመላክቶናል::

የየካ ክፍለከተማ ወረዳ 01 /ፈረንሳይ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ/ ነዋሪዋ ወይዘሮ ካሰች መኩሪያ ማሻሻያው ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት አንድ ኪሎ ጤፍ 130 ብር ይሸጥ እንደነበር ያስታውሳሉ:: እሱም ይሁን ብለን እየገዛን ነበር ያሉት ወይዘሮ ካሰች፣ አሁንም ዋጋው ጨምሮ 170 ደርሷል፤ ከቀነሰ ብዬ መግዛቱን ትቼዋለሁ ብለዋል:: የዋጋ ንረቱ በዚሁ ከቀጠለ እና ቁጥጥር ካልተደረገበት ቀጣዩ ጊዜ እንደሚያሰጋቸው ይገልጻሉ ::

ማሻሻያው መደረጉን ተከትሎ በተለያዩ ምርቶች ላይ አላግባብ ጭማሪ በሚያደርጉ ነጋዴዎች ላይ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ እርምጃ እየወሰድኩ ነው ማለቱን ጠቅሰን፤ ይህን ተከትሎስ ምን ለውጦች አሉ ስንል ላነሳንላቸው ጥያቄም የጤፍ ዋጋ በአንዳንድ ወፍጮ ቤቶች እና አቅራቢዎች በፊት ከነበረው ትንሽ የቀነሰበት ሁኔታ እንደነበር ተናግረው፣ በፊት ይሸጥበት ከነበረው ዋጋ ግን የጨመረ መሆኑን ጠቁመዋል:: ወይዘሮ ካሰች በሌሎች ምርቶች ላይ የሚታየውን የዋጋ ጭማሪ ለማረጋጋት ቁጥጥሩ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም ገልጸዋል ::

ሌላኛዋ የሁለት ልጆች እናት ወይዘሮ ወይንሸት አይቼው በበኩሏ፤ በየእለቱ የምትጠቀማቸውን ምርቶች ለመግዛት ሁልጊዜ ወደ ምትገዛበት ሱቅ ብትሄድም አንድ ሺህ 50 ብር ይሸጥ የነበረው የአምስት ሊትር ዘይት ዋጋ 1500 ብር ሆኖ አግኝታዋለች:: እንደ ምስር ፣ ሩዝ፣ ፓስታ፣ ማካሮኒ እና ሌሎች ምርቶች እንዲሁ ከሌላው ጊዜ በተለየ የዋጋ ጭማሪ ማሳየታቸውን ታስታውሳለች:: « ምናልባት ሌሎች ሱቆች ላይ ሊቀንስ ይችላል ብዬ ብሄድም አንዳንድ ሱቆች ላይ እንዲያውም ምርቶቹ የሉም ብለው መልሰውኛል» በማለት አብራርታለች ::

የዋጋ ማሻሻያውን ተከትሎ በአንዳንድ የንግድ ሱቆች ላይ የተስተዋለው ይህ የዋጋ ጭማሪ ወደ ነበረበት እንዲመለስ በተደረገው ቁጥጥር ለውጦች የመጡበት ሁኔታ እንዳለም ወይዘሮ ወይንሸት ገልጻለች:: ዋጋው በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ የነበረው ዘይት አንዳንድ ሱቆች ላይ ዋጋው ወደ ነበረበት መመለሱን ጠቅሳለች :: የዋጋ ጭማሪውን ለመግታት ቁጥጥር ከማድረግ ባለፈ በየአካባቢው በሚገኙ የሸማች ሱቆች ላይ ምርቶች ቢቀርቡ የተሻለ መሆኑን ወይዘሮ ወይንሸት አመልክታለች::

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ከመደረጉ አስቀድሞ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለመግዛት በተለያዩ የአዲስ አበባ ከተሞች የቅዳሜ እና እሁድ ገበያ በሚል አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎች መሸመት የምታዘወትረው ወይዘሮ ሰናይት ሹምዬ በበኩሏ « ከዚህ በፊት 45 ብር እና 50 ብር ይሸጥ የነበረው ሽንኩርት በእጥፍ ጨምሮ 120 ብር ገብቷል» ብላለች:: 30 ብር እና 25 ብር የነበረው ቲማቲምም እንዲሁ 70 እና 90 ብር እየተሸጠ መሆኑን አስታውቃለች::

**በዚህም ባለፈው ሳምንት 273 ኩንታል ዱቄት ፣ ሩዝ፣ እንዲሁም ዘይት እና ስኳር የጫኑ ተሽከርካሪዎች እንዲገቡ ተደርጓል :: የተለያዩ ብራንዶች ያሉት 20 ሺህ ካርቶን ዘይት ባለ 5 ሊትር እንዲሁም በመርካቶ ገበያ እንዲራገፍ ተደርጓል**

በዋጋ ጭማሪው ምክንያት መግዛት የምትፈልገውን የምርት መጠን ወደ ግማሽ ለማድረግ እንደወሰነችም ትገልጻለች:: « በቅዳሜ እና እሁድ ገበያ ላይ ከዚህ በፊት እሁድ ምሽት ድረስ በቂ አቅርቦት ነበር፤ አሁን ግን እነሱም አንዳንድ አትክልቶችን በጊዜ ጨርሰናል » በማለት በእነዚህ ስፍራዎች ላይ የአቅርቦት እጥረት መኖሩንም ጠቅሳለች:: በተለያዩ የንግድ ሱቆች ላይ ገበያውን ለማረጋጋት እየተደረገ በሚገኘው ክትትልና ቁጥጥር አስቀድሞ እንደነበረው ባይሆንም አሁን ላይ ሽንኩርትም 90 ብር እየተሸጠ እንደሆነ ገልጻለች ::

በቀጣይ ይህን መሰሉን የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ ለመቆጣጠር ይበጃል ያለችውን መፍትሄ ሰንዝራለች:: « ቁጥጥሩ ሰው በብዛት በሚኖርበት አካባቢ በሚገኙ ሱቆች ላይ ቢደረግ መልካም ነው፤ ምክንያቱም እኛ በየቀኑ የምንጠቀመው ከዚያ ነው» ስትል ገልጻ፤ በቅዳሜ እና እሁድ ገበያ ላይ በቂ ምርቶች እንዲቀርቡ ማድረግ እንደሚገባም አስታውቃለች:: ለእዚህም የሚመለከተው አካል ትኩረት እንዲሰጠው ጠይቃለች::

የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሰውነት አየለ « አብዛኛው ነጋዴ ህግና ሥርዓትን ተከትሎ እንደሚሰራ ጠቅሰው፣ ህገወጥ ነጋዴዎች ግን የተደረገውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተከትሎ በገበያው ላይ ሰው ሰራሽ እጥረት በመፍጠር ምርቶች ላይ የዋጋ ጭማሪ ሲያደርጉ ይስተዋላል ብለዋል:: ቢሮው እነዚህን ህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች ለመቆጣጠር ግብረ ኃይል አቋቁሞ እየሰራ መሆኑን አስታውቀዋል::

እሳቸው እንዳሉትም፤ ማሻሻያውን ተከትሎ በህገወጦች የተደረገውን የዋጋ ጭማሪ ተከትሎ ቢሮው ባደረገው የቁጥጥርና ክትትል ስራ የተለያዩ የንግድ ሱቆች በተለያዩ ምርቶች ላይ የዋጋ ጭማሪ አድርገው ተገኝተዋል:: የዋጋ ጭማሪ ባደረጉት ላይም እርምጃ እየተወሰደባቸው ነው::

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ከተደረገ በኋላ የንግድና ግብይት እንቅስቃሴው ህግ እና ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን የተለያዩ ስራዎች ተሰርተዋል:: ቢሮው በህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተው ተገኙ ባላቸው 769 የሚጠጉ የንግድ ሱቆች ላይ እርምጃ ወስዷል :: ከእነዚህ ውስጥም 340 የሚሆኑት አለአግባብ ዋጋ በመጨመር የተስተዋለ የንግድ እንቅስቃሴ ሲሆን፣ በዚህም ሱቆቹ እንዲታሸጉ ተደርጓል :: 423 የሚደርሱ ምርትን በማሸሽ፣ በመደበቅ እና የዋጋ ዝርዝር ባለመለጠፍ በገበያው ላይ እጥረት እንዲፈጠር ሲያደርጉ በቁጥጥር ስራው ተደርሶባቸዋል::

ቢሮው ከማዕከል እስከ ወረዳ በመቀናጀት ጠንካራ የሆነ ክትትል እና ቁጥጥር እያደረገ እንደሚገኝም ገልጸዋል ::

ከዋጋ ጭማሪው በተጨማሪ አንዳንድ መደብሮች ደግሞ ምርቶች የሉም የሚል ምላሽ እየሰጡ መሆናቸውን በመጥቀስ ይህን ችግር ለመፍታት እየተከናወነ ስላለው ተግባር የጠየቅናቸው የኮሙኒኬሽን ኃላፊው «ይህንንም ችግር ለመፍታት በከተማው ላይ የምርት መሸሽግ ሊደረግባቸው ይችላሉ በተባሉ መጋዘኖች ላይ ፍተሻ እየተደረገ ይገኛል» ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል:: ቢሮው በሚያደርገው የክትትልና ቁጥጥር ስራ በአዲስ አበባ ዙሪያ ወደሚገኙ ከተሞች ምርቶችን የማሸሽ ሁኔታ መኖሩን ገልጸው፣ ይህንንም ችግር ለመፍታት ከኦሮሚያ ክልል እና ከክልሉ የሸገር ሲቲ አስተዳደር ጋር በመሆን ፍተሻዎች መደረጋቸውንም አስታውቀዋል:: በተደረገው ፍተሻም በቡራዩ በሶስት መጋዘኖች ላይ ክምችት ተገኝቶ እንዲታሸግ ተደርጓል ብለዋል::

ይህ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለአንዳንዶች አዲስ ሃሳብ መሆኑን ጠቅሰው፣ ቢሮው በንግድ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ህጎችን አክብረው በማይሰሩ ላይ እርምጃ ከመውሰድ ባለፈ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እየሰራ ይገኛል ብለዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የታለመለትን አላማ እንዲያሳካ ቢሮው ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ እየሰራ ነው፤ በተለይ በምርት አቅርቦት ላይ እየሰራ ይገኛል:: ከኢትዮጵያ ጉምሩክ ፣ ከኢትዮጵያ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እንዲሁም ከኦሮሚያ ክልል ጋር በመሆን አዳማ ፣ ጅግጅጋ እና ሰመራ ከተሞች ላይ በተለያየ ምክንያት ቆመው የነበሩ ምርት የጫኑ መኪኖች ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ እየተደረገ ነው:: በዚህም ባለፈው ሳምንት 273 ኩንታል ዱቄት ፣ ሩዝ ፣ እንዲሁም ዘይት እና ስኳር የጫኑ ተሽከርካሪዎች እንዲገቡ ተደርጓል :: የተለያዩ ብራንዶች ያሉት 20 ሺህ ካርቶን ዘይት ባለ 5 ሊትር እንዲሁም በመርካቶ ገበያ እንዲራገፍ ተደርጓል ::

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የንግድ ስራው ህግና ሥርዓቱን ተከትሎ እንዲካሄድ ለማስቻል እንዲሁም በሌላ በኩል የምርት አቅርቦት በበቂ ሁኔታ እንዲኖር እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ያለውን የግንዛቤ ክፍተት ለመሙላት እየሰራ መሆኑን ኃላፊው አስታውቀዋል::

ማህበረሰቡም በህገ - ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ በሚገኙ ነጋዴዎች ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎችን እንዲደግፍ ጠይቀው፣ ህብረተሰቡ ቢሮው ህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር በሚሰራው ስራ እንዲሳተፍ 8588 ነጻ የስልክ መስመር ይፋ አድርጎ እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል ::

በተለያዩ የንግድ ሱቆች በዘይት እና ሌሎች ምርቶች ላይ የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ ነጋዴዎች እና ምርት በማሸሽ እና በመደበቅ የዋጋ ንረት እንዲፈጠር በሚያደርጉ ነጋዴዎች ላይ አሁንም ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ምግብና መጠጥ በሚያቀርቡ የገበያ ማዕከላት ላይ ቁጥጥር እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል:: ህብረተሰቡ የከተማ አስተዳደሩ ባስገነባቸው የገበያ ማዕከላት በመሄድ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት እንደሚችልም አቶ ሰውነት ጠቁመዋል ::

የምርት አቅርቦት ከተማ ውስጥ በስፋት እንዲኖር በማድረግ እና ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን በመቆጣጠር ግንዛቤዎችን በማስፋት እና ህገወጥ እንቅስቃሴዎች ሲመለከት ህብረተሰቡ የሚጠቁምባቸውን መንገዶች በመፍጠር የገበያ አለመረጋጋቱን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የማክሮ ኢኮኖሚውን ማሻሻያውን ምክንያት በማድረግ የንግድ ሥርዓቱን በማዛባት ወደ ሕገወጥነት የገቡ አካላት ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ እና የተመቻቸላቸውን ሕጋዊ የአሠራር ሥርዓት ተከትለው እንዲተገብሩ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አሳስቧል።

የአገልግሎቱ ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) ሰሞኑን በሰጡት መግለጫ፤ ማሻሻያውን ምክንያት በማድረግ ወደ ሕገ ወጥነት በመግባት የንግድ ሥርዓቱን ለማዛባት የሚሞክሩ አካላት ከድርጊታቸው ሊታቀቡ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ምክንያት ምንም አይነት የዋጋ ጭማሪ ለማድረግ የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ እንደሌለም አስገንዝበዋል።

ማሻሻያው በተሟላ መልኩ ወደተግባር ሲገባ ጥቂት ስግብግብ ነጋዴዎች በከተሞችና በክልል ከተሞች የሚፈጥሩት ሕገወጥነት እየተስተዋለ መሆኑን በመጥቀስ፤ እነዚህ አካላት ከድርጊታቸው ሊታቀቡ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ድርጊቱ ምክንያታዊ መሠረት የሌለው መሆኑንም በመጥቀስ ተቀባይነትም እንደማይኖረው ሚኒስትሩ አስታውቀዋል። መንግሥት የቁጥጥር ሥራ በማከናወን ሱቆችን የማሸግና ነጋዴዎቹም ላይ እርምጃ በመውሰድ ላይ መሆኑንም ገልጸዋል። አብዛኞቹ ነጋዴዎች የማሻሻያውን አስፈላጊነት በመረዳት ሥርዓቱን ተከትለው የንግድ እንቅስቃሴን በማከናወን ላይ እንደሚገኙም አስረድተዋል። ትግበራው ፋይናንሻል መረጋጋት ለማምጣት፣ የልማት ፕሮጀክት ውጤታማነትን እንዲሁም የመንግሥትን ገቢ ለማሻሻል ያለመ መሆኑንም አመልክተዋል።

መዝናኛ

ማረፊያ/ትዝብት

# የትርክት ዕዳ እና ድህነት

**ዋስልኝ አየለ**

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት የጻፈው ‹‹የትርክት ዕዳና በረከት›› መጽሐፍ ባለፉት ሳምንታት አጀንዳ ሆኖ ቆይቷል:: በፋና እና በዋልታ ቴሌቪዥን ቀርቦ ለጥያቄዎች መልስና ማብራሪያ ሰጥቷል:: ከመጽሐፉም ሆነ ከጸሐፊው ተጨማሪ ማብራሪያዎች (በቃለ መጠይቆች) የምንረዳው ነገር የትርክት ዕዳ ምን ያህል ወደ ድህነት እንደሚወስደን ነው:: የመጽሐፉን ይዘት በተመለከተ በሌላ ዓምድ የሚታይ ስለሚሆን ለዛሬው ግን ትርክት ላይ ያለኝን ትዝብት ላጋራ::

እስኪ ፖለቲከኞቻችንን ልብ በሉ! መድረክ ባገኙ ቁጥር፣ በመገናኛ ብዙኃን ለቃለ መጠይቅ በተጋበዙ ቁጥር፣ በብዛት የሚያወሩት ስለምንድነው? በሀገሪቱ ውስጥ ስለሚባክነው ሀብት ያወራሉ? ይህን እምቅ ሀብት ይዘን ለምን ድሃ ሆንን ብለው ይቆጫሉ? ስለጤና እና የኢኮኖሚ ዘርፎች ያወራሉ?

ሁሉም ለማለት በሚያስችል ሁኔታ የሚያወሩት ‹‹እገሌ እገሌን በድሏል›› የሚል ነው:: አሁን ላለ ችግር ያለፈውን መርገም ነው:: 100 እና 200 ዓመት ወደኋላ እየተመለሱ እገሌ የእገሌን ዘርያ ጨፍጭፏል የሚል ነው:: እገሌ የሚባል ዓፄ እዚህ ቦታ እንደዚህ አድርጓል የሚል ነው:: ይህን አጀንዳ በጣም ከመደጋገማቸው የተነሳ ወጣቱ ትውልድም በዚሁ ትርክት ተቀረጸ:: ስለዚህ የጋራ ማንነት እንዳይኖር አደረጉ ማለት ነው:: ወደ ግጭት ሄድን ማለት ነው:: ግጭቶች ደግሞ ለድህነት ዳረጉን ማለት ነው::

ዓለም እያወራና እየሠራ ያለው ስለወደፊቱ ነው:: 22ኛው ክፍለ ዘመን ምን ሊሆን ይችላል? እየተባለ ነው:: ያለፈውን ዘመን የሚጠቀመው ከዚህ ነው የተነሳን ለማለት ብቻ ነው:: የሠለጠነው ዓለም ከ100 እና 200 ዓመት በፊት በነበረ ድርጊት አይጨቃጨቅም:: በ22ኛው ክፍለ ዘመን ምን አይነት የሰው ልጅ አኗኗር እንደሚኖር እያሰበ ነው::

እኛስ? እኛ ደግሞ የምናስበው ስለ 22ኛው ክፍለ ዘመን ትውልድ ሳይሆን ስለ 19ኛው ክፍለ ዘመን ትውልድ ነው:: ወደፊት ሳይሆን ወደኋላ ማለት ነው:: ሁልጊዜ ወደኋላ ብቻ የምናስብ ከሆነ ትውልዱ ዘመናዊ አይሆንም:: በትርክትና ጥላቻ የተበረዘ ይሆናል:: በጥላቻ ትርክት ከተበረዘ ደግሞ ወደ ግጭት ያመራል ማለት ነው:: ግጭት ደግሞ በተዘዋዋሪ ሳይሆን በቀጥታ ድህነት ላይ ይጥለናል::

ግጭት ድህነት ላይ ይጥለናል ሲባል በጦርነቱ የሚወድመው ንብረት ብቻ አይደለም:: እንዲያውም በጦርነቱ በቀጥታ ከሚወድመው በላይ አደገኛ የሚሆነው ሥነ ልቦናዊና አካባቢያዊ ጫናው ነው:: በግጭቶች ምክንያት ሰዎች ሥራ ለመሥራት አያስቡም:: የረጅም ጊዜ ዕቅድ አይኖራቸውም:: እስኪ ወደዚህ አካባቢ ሄጄ እንዲህ አይነት ሥራ ልሥራ፣ ይህን ከዚህ አካባቢ ገዝቼ እዚህኛው አካባቢ ልሸጥ.... የሚሉ የሥራ ሀሳቦች አይኖሩም:: ይህ የሚሆነው ግጭቶች ባሉበት አካባቢዎች ብቻ ሳይሆን ምንም ግጭት በሌለባቸው አካባቢዎችም ጭምር ነው:: ምክንያቱም ሀገራዊ አጀንዳው እገታና ጦርነት ከሆነ የሥራ ወኔዎች ይቀዛቀዛሉ:: ለምሳሌ፤ በመዝናኛው ዘርፍ በኩል ያሉ የሥራ ዘርፎች ይቀዘቅዛሉ:: ስለዚህ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እየተፈጠረ ነው ማለት ነው::

ይህ ሁሉ የሆነው እንግዲህ በፖለቲከኞች የትርክት ዕዳ ነው:: የማያውቀውን የ10ኛ ትውልድ ዝርያውን እየጠሩ እገሌ እንዲህ አድርጎብሃል እያሉ አዕምሮው ላይ በሠሩት ሥራ ነው:: በሠላም ይኖር የነበረውን ኅብረተሰብ በጥርጣሬ እንዲተያይ በማድረጋቸው ነው:: ገዥ መንግሥታትን ከአንድ አካባቢ ሕዝብ ጋር በማያያዝ ‹‹እነርሱ ናቸው›› የሚል የተሳሳተ ትርክት በመዘርጋቱ ነው::

እኔ ስለ ዛሬው እና ስለ ነገው ነው ማሰብ ያለብኝ:: ከ200 ዓመት በፊት ከነበረ አንድ የእኛ ሰፈር ሰው፤ ዛሬ ላይ በሕይወት ያለ የሞያሌ ሰው ይቀርበኛል:: ምክንያቱም የዚህ ትውልድ ሰዎች ነን:: እኔ የመሐል ሀገሩ ሰውና አንድ የሞያሌ ወይም የዓዲግራት ወይም የመተማ ሰው ብዙ የሚያገናኘን ነገር አለ:: ብዙ የጋራ ነገር አለን:: እኔና ከ200 ዓመት በፊት የነበረው ሰውየ ግን ምንም የሚያገናኘን ነገር የለም:: ያ ዘመን እና አሁን እኔ ያለሁበት ዘመን ሌላ ዓለም እና ሌላ ዓለም ማለት ነው:: ሳይንቲስቶች እንደሚሉት ከ800 ሺህ ዓመት በፊት ገና በሁለት እግር ቆሞ መሄድ የጀመርንበት ነበር:: ከዚያ በፊት ዝንጀሮ መሳይ ነበርን:: ስለዚህ ጊዜው እየራቀ በሄደ ቁጥር ጭራሽ ሌላ ዝርያ እና ሌላ ዝርያ ሁሉ ልንሆን እንችላለን ማለት ነው:: ታዲያ በምን ዕዳዬ ነው ከመቶ ምናምን ዘመናት በፊት በነበሩ ሰዎች ጣጣ እኔ የምጨቃጨቀው? ምን አይነት ኋላቀርነት ነው?

ያለፈ ዘመን ለጥናትና ምርምር፣ ከዚህ ተነስተን እዚህ ደረስን... ለማለት ነው እንጂ መዋል ያለበት፤ በዚያኛው መነጽር የዛሬውን ለማየት አይደለም:: ያ ዘመን እና ይህ ዘመን አይነፃፀርም:: ደርሶ የእገሌ ዘር ነኝ ማለት ልክ አይሆንም::

በጥንት ዘመን የሰው ልጅ በለቀማ እና በአደን ይኖር ነበር:: አደን ማለት ልክ እንደ ዛሬው ሕክምና፣ ምሕንድስና፣ ፓይለት... አንድ የሥራ ዘርፍ ነበር:: የሚኖረው በማደን ነበር:: ዛሬስ? ዛሬ ነውር ነው፤ የእንስሳት መብት ጠባቂ ተቋማት ተፈጥረዋል:: ብዙ እንስሳት የቤት ሆነው ተላምደዋል:: የዱር የሆኑትም ጥብቅ እና ብርቅዬ ተብለው ጥበቃ እየተደረገላቸው ነው:: ይህ በሥልጣኔ የመጣ ነው::

ልክ በዚህ የዘመን ቅደም ተከተል መሠረት ከመቶ ምናምን ዘመናት በፊት ጨካኝ ድርጊቶች ቢኖሩ ይገርማል ወይ? ሰብዓዊ ሥነ ልቦናዊ ከዛሬው ጋር ይነፃፀራል ወይ? በዛሬ መነጽር ለምን እናየዋለን? ሲቀጥል ደግሞ እኛ ከሺህ ዘመናት በፊት ከነበረው እየባስን አይለም ወይ? ሰው ከነነፍሱ ሲቃጠል እያየን አይደለም ወይ? ከዚያኛው ይልቅ ለምን ይህኛው አልቆጨንም፣ አላስገረመንም?

የድሮ ነገር ትርክት ላይ መሟጨጭ የሰነፎች ነው:: ስለዛሬው ማሰብ የማይችሉ ሰዎች የሚያደርጉት ነው:: ዘመኑ የደረሰበት ልዕልና ላይ ያልደረሱ ሰዎች የሚያደርጉት ነው:: ‹‹ያኔ እንዲህ ተደርጎ ነበርና...›› ማለት የዛሬውን መረዳት አለመቻል ነው::

ወዲህ ደግሞ በድሮ ነገር መፎከርም እልም ያለ ስንፍና ነው:: ለምንድነው ከ100 ዓመት በፊት በነበረ ሰው የሚፎክር? ፉከራው ብቻ እኮ አይደለም ችግሩ! ጭራሽ የሚፎክርባቸው ሰዎች ካደረጉት በተቃራኒው ሆኖ መፎከሩ ነው እንጂ:: የእነርሱን ሰብዓዊነትም ሆነ አስተዋይነት የሌለው መሆኑ ነው:: ከ100 እና ከ200 ዓመት በፊት በነበሩ ሰዎች ስም እየፎከረ እሱ ግን ከእነርሱ ያነሰ ሰብዓዊነትና አስተዋይነት ያለው ነው::

የሰው ልጅ በየዘመኑ የራሱን መልክና ቅርጽ ይይዛል:: ከዛሬ 100 ዓመት በኋላ ምናልባትም ሁላችንም አንኖርም፤ ይህንንም እያሰብን::

ስንፍናችን ከብዙ ዘመናት በፊት የነበረው ላይ ብቻ አይደለም:: ትናንት ያየነውን፣ በሕይወት ኖረን ያሳለፍነውን ሁሉ እንክዳለን:: ይህም በትርክት ጫና የሚመጣ ነው:: የኖርኩበትን ዘመን ማንም ሊያጭበረብረኝ አይችልም:: ብዙ ፖለቲከኞች ግን ራሳቸውን የጥፋቱ አካል ከማድረቅ ይልቅ እገሌ እንዲህ ስላደረገብኝ ነው የሚል ሰበብ ይፈልጋሉ:: ገዥ መንግሥትን ከሕዝብ ጋር በማገናኘት ‹‹ተረኝነት፣ ወገንተኝነት፣ የእነ እገሌ የበላይነት...›› በማለት ሕዝብ ጭምር በጥርጣሬ እንዲተያይ ያደርጋሉ:: አንድ መንግሥት መወቀስ ካለበት አመራርነት ላይ ያሉትን እንጂ ተራው ሕዝብም ምን አድርጓል?

ለሚመጣው ትውልድ የሚሆን ነገር ነው ማስቀመጥ ያለብን:: ለትልውድ ነው የምንሠራው ካልን የምናደርገው ነገር ለትውልድ ይሆናል ወይ? የሚለውን ልብ ማለት አለብን:: ስለዚህ የትርክት ዕዳ ከድህነት ወደ ድህነት እየወሰደን ነውና ለትውልድ እናስብ!

# ዓለም አቀፍ

## የሱዳን ጦር እንደሚሳተፍ ማረጋገጫ ያልሰጠበት ድርድር በነገው ዕለት በጄኔቫ ይካሄዳል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ለ16 ወራት የቆየውን የሱዳን ግጭት ለማስቆም ሁለቱን ተፋላሚዎች ለማቀራረብ የሚደረገው ድርድር በነገው ዕለት በጄኔቫ መካሄድ ይጀምራል::

የሱዳን ሠራዊት በድርድሩ ላይ እንደሚሳተፍ ማረጋገጫ ባይሰጥም ድርድሩ በተያዘለት ቀጠሮ እንደሚካሄድ አሜሪካ አስታውቃለች::

በአሜሪካ እና ሳዑዲ ዓረቢያ መሪነት በሲውዘርላንድ ጄኔቫ እንዲካሄድ ለቀረበው የድርድር ጥሪ የሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መንግሥት ፈቃደኛ መሆኑን አስታውቆ እንደነበር ይታወሳል::

የሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለፈው የፈረንጆቹ ወር መጨረሻ ላይ ባወጣው መግለጫ ከፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ጋር ለመደራደር ፈቃደኛ ነኝ ቢልም፤ ተቀናቃኝ የሆኑት ሀምዳን ዳጋሎ የሚመሩት ጦር ከተቆጣጠራቸው ስፍራዎች እንዲለቅ እና ሌሎች አካባቢዎችን ለመቆጣጠር የሚያደርገውን ውጊያ እንዲያቆም ቅድመ ሁኔታ አስቀምጧል::

በተጨማሪም በድርድሩ አጀንዳዎች ዙሪያ ከአሜሪካ ባለሥልጣናት ጋር መነጋገር እንደሚፈልግ ገልጿል::

ይህን ተከትሎ በሳዑዲ ዓረቢያ ጂዳ የሱዳን ጦር ባስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ምክክር ሲደረግ ቢቆይም በሳምንቱ መጨረሻ እሁድ ያለ ስምምነት ተበትኗል::

በሱዳን የአሜሪካ ልዩ መልዕክተኛ ቶም ፔሪዬሎ ከሱዳን ጦር ጋር ሲደረግ የነበረው ምክክር ያለ ስምምነት መጠናቀቁን ተከትሎ የጦሩ ተወካዮች በነገው ዕለት በሚጀምረው ጉባኤ ላይ እንደሚሳተፉ ማረጋገጫ ባይሰጡም ጦርነቱን ለማስቆም የሚደረገው ዓለምአቀፋዊ ጥረት አካል የሆነው የጄኔቫው ድርድር ይካሄዳል ብለዋል::

ልዩ መልዕክተኛው አክለውም በሱዳኑ ግጭት ዙሪያ አፋጣኝ ተኩስ አቁም እና ድርድር የማይካሄድ ከሆነ የተራዘመው ጦርነት ሀገሪቱን ሊያፈርሳት ይችላል ነው ያሉት::

በንጹሐን ላይ በሚደርስ በደል እና የሰብዓዊ መብት ጥሰት በተደጋጋሚ የሚከሰሰው የፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ መሪ ጄነራል ሃምዳን ዳጋሎ ንጹሐንን የሚጠብቅ አዲስ የፀጥታ ኃይል ማቋቋማቸውን አስታውቀዋል:: በተጨማሪም ጄኔራሉ በነገው ጉባኤ ላይ ልዑካቸው እንደሚካፈል አረጋግጠዋል::

ሮይተርስ እንደዘገበው የፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ በተለያዩ ስፍራዎች የሚያደርሳቸውን የተጠናከሩ ጥቃቶችን ቀጥሏል:: በቅርብ ቀናት ከዋና ከተማዋ ቅርብ ርቀት ላይ በምትገኘው ኦምዱርማን በፈጸመው ጥቃት 40 የሚጠጉ ሰዎች ላይ ጉዳት ደርሷል::

16 ወራትን ባስቆጠረው ጦርነት 10 ሚሊዮን ሰዎች ከቀያቸው ሲፈናቀሉ በ10 ሺዎች እንዲገደሉ ምክንያት ሆኗል::

የቅርብ ጊዜ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ሱዳን ካሏት 18 ክልሎች ውስጥ ስምንቱ በፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ቁጥጥር ስር ይገኛሉ::

በነገው እለት ጄኔቫ የሚካሄደው ድርድር በአሜሪካ እና ሳዑዲ መሪነት የሚደረግ ሲሆን የአፍሪካ ኅብረት፣ ግብፅ እና ዓረብ ኢምሬትስ በታዛቢነት እንደሚታደሙ ተገልጿል::

## ብሪታንያ ኢራን በእሥራኤል ላይ ጥቃት ከመሰንዘር እንድትታቀብ ጠየቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የብሪታንያው ጠቅላይ ሚኒስትር ኪር ስታርመር ኢራን በእስራኤል ላይ ለመፈጸም ያሰበችውን የአጸፋ ምላሽ እንድታቆም ጠየቁ::

የሀማስ የፖለቲካ ቢሮ ኃላፊ እስማኤል ሀኒየህ በቴህራን መገደሉን ተከትሎ በቴልአቪቭ ላይ ከኢራን ይፈጸማል ተብሎ የሚጠበቀው የአጸፋ ምላሽ እየተጠበቀ ነው::

ይህን ተከትሎም ቀጣናው ወደለየለት ጦርነት ሊመራ እንደሚችል ከፍተኛ ስጋት አንዣቧል::

ኪር ስታርመር ከኢራኑ ፕሬዚዳንት ጋር ባደረጉት የስልክ ውይይት የአጸፋ ጥቃቱ ከፍተኛ አደጋን የሚያስከትል የጋዛውን ጦርነት ማብቂያም ሊያራዝም የሚችል ሁነት በመሆኑ በጉዳዩ ላይ እንዲያጤኑበት ጠይቀዋል::

የቀድሞው የብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ከቀድሞው የኢራን ፕሬዚዳንት ሀሰን ሩሀኒ ጋር በ2021 ካደረጉት የስልክ ንግግር ቀጥሎ ከሦስት ዓመታት ወዲህ የሁለቱ ሀገራት መሪዎች በቀጥታ ሲነጋገሩ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው::

ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን እና አሜሪካ ኢራን በእስራኤል ላይ ጥቃት ከመሰነዘር እንድትታቀብ የጋራ መግለጫ ካወጡ በኋላ ሁለቱ መሪዎች ለ30 ደቂቃ የስልክ ውይይት አድርገዋል::

ምዕራባውያኑ በጋራ ካወጡት መግለጫ ባለፈ እሥራኤል ከኢራን እና በሽብርተኛነት ከተፈረጁ ታጣቂ ቡድኖች የሚሰነዘርባትን ጥቃት መመከት ትችል ዘንድ እገዛ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል::

የኢራን እና የብሪታንያ መሪዎች በነበራቸው የስልክ ቆይታ ከጋዛው ጦርነት ባለፈ በኢራን የኒውክሌር ፕሮግራም ዙሪያም መክረዋል::

ለዘብተኛ የሚባሉት አዲሱ የኢራን ፕሬዚዳንት መሱድ ፔዚሽኪያን ሀገራቸው ከምዕራቡ ዓለም ጋር የገባችበትን ውጥረት ለማርገብ እና ግንኙነታቸውን ለማሻሻል ቃል ገብተዋል::

ቢቢሲ እንደዘገበው ፕሬዚዳንቱ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ሁኔታዎችን ለማሻሻል ከሚወስዷቸው ርምጃዎች መካከል እሥራኤል ላይ የሚሰነዘረውን ጥቃት ማስቀረት አንዱ ሊሆን ይችላል::

ሆኖም ውሳኔው ከፕሬዚዳንቱ ባለፈ የሃይማኖታዊ መሪውን አያቶላ አሊ ሀሚኒን ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል::

የኢራን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባሳለፍነው ሳምንት ባወጣው መግለጫ በእሥራኤል ላይ ጥቃት የመሰነዘር እቅድ እንዳልተቀየረ እና በትክክለኛው ሰዓት እና ቦታ ተመጣጣኝ እርምጃ እንደሚወሰድ አረጋግጧል፡

አሜሪካ በበኩሏ በቀጣናው ከፍተኛ የጦር መሣሪያዎችን እና የውጊያ መርከቦችን ያስጠጋች ሲሆን በትላንትናው እለት 154 የቶምሃውክ ክሩስ ሚሳኤሎችን ማስወንጨፍ የሚችለውን ሰርጓጅ መርከብ ወደ ቀጣናው ልካለች::

ቴህራን በእሥራኤል ላይ ምን አይነት ጥቃት ልትሰነዝር እንደምችል ቦታው እና ጊዜው እስካሁን ባይታወቀም እሥራኤል እና አጋሮቿ ሊሰነዘር የሚችለውን ጥቃት ለመከላከል ከፍተኛ ዝግጅቶችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ::

በመጪው ሐሙስ የእሥራኤል እና የሀማስ መሪዎች በተኩስ አቁም እና ታጋቾችን በማስለቀቅ ዙሪያ በአፋጣኝ እንዲደራደሩ በቀረበላቸው ጥሪ መሠረት በድርድሩ በጎ ውጤት የሚገኝ ከሆነ የቀጣናውን ውጥረት በመጠኑም ቢሆን ሊያረግበው እንደሚችል ይጠበቃል::

# ኮስታራው አሠልጣኝ- ዶክተር ወልደመስቀል ኮስትሬ

ክብረአብ በላቸው

ኢትዮጵያ የጀግኖች ሀገር ነች፡፡ በጦር ሜዳ ብቻ በየተሰማሩበት መስክ ሁሉ ደምቀው ኢትዮጵያን ያደመቁ፤ የሕዝብን አንገት ቀና ያደረጉ በርካታ ብርቅዮችን ከማሕፀኗ አፍርታለች፡፡ እነዚህ ጀግኖች በተነሱ ቁጥርም የኢትዮጵያ ስምም አብሮ ይነሳል፡፡

ሀገራቸውን ከውጭ ወራሪና ጠላት በመከላከል አኩሪ ታሪክ የሠሩ፣ የሕዝባቸው ደኅንነትና አንድነት እንዲጠበቅ ለማድረግ መስዋዕትነት የከፈሉና አንፀባራቂ ታሪክ የሠሩ ጥቂቶች አልበሩም፡፡ በደራሲነት፣ በሙዚቃ፣ በሥዕል፣ በስፖርት፣ በታሪክ፣ በሳይንስና በእምነት አስተምሮ፣ የኪነ ጥበብና የምርምር ሥራዎችም ኢትዮጵያን በዓለም የበለጠ እንድትታወቅ ያደረጉ ትናንትናም ዛሬም ደምቀው የሚታዩ ደማቅ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብዙዎች ናቸው፡፡

ከእነዚህ የሀገር ባለውለታ ግለሰቦች መካከል ኢትዮጵያ በስፋት በምትታወቅበት የአትሌቲክስ ስፖርት በተለይ በረዥም እርቀት አትሌቲክስ ሥልጠና ጉልህ ተሳትፎ የነበራቸውና የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በዓለም አደባባይ ማውለብለብ የቻሉ ዘመን አይሽሬ ስመ ጥር አትሌቶችን በውጤታማ አሠልጣኝነት ማፍራት የቻሉት ወልደመስቀል ኮስትሬ (ዶ/ር) በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ።

ወልደመስቀል ኮስትሬ (ዶ/ር) ጥር 21 ቀን 1939 ዓ.ም. በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ልዩ ስሙ ወንፈስ በተባለ ሥፍራ ነበር የተወለዱት። ዕድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ የቤተ-ክህነት ትምህርት ተከታትለዋል። በመቀጠልም የትውልድ አካባቢያቸውን ለቀው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በቀድሞ ስያሜው አስፋወሰን ይባል በነበረው ት/ቤት በመግባት መደበኛ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል።

በነበራቸው የስፖርት ተሳትፎም ትምህርት ቤታቸውን እየወከሉ በ400፣ 800 እና 1500 ሜትር ይወዳደሩ ነበር። ቀጥሎም በመምህራን ማሠልጠኛ ገብተው በስፖርት ትምህርት በመሠልጠን እንደጨረሱ በዚያው በተማሩበት ት/ቤት በመምህርነት ሠልጥነው በዚያው ሲያገለግሉ ቆዩ።

ወልደመስቀል (ዶ/ር) በ1956 ዓ.ም. የውጭ የትምህርት ዕድል አግኝተው ወደሀንጋሪ በመሄድ የተማሩ ሲሆን በዚያው ሀገር ቆይታቸው የሚማሩበትን ኮሌጅ እየወከሉ በ5,000 እና በ 10,000 ሜትሮች መወዳደራቸው ታውቋል። በ1963 ዓ.ም. በስፖርት ሳይንስ የማስተርስ ዲግሪያቸውን ይዘው ወደ ሀገራቸው በመምጣት በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ እያስተማሩ በተደራቢ በአትሌቲክሱ ዘርፍ የብሔራዊ ቡድኑን ከሚያሠለጥኑ አንዱ በመሆን ሠርተዋል።

በ1966 ዓ.ም. እንደገና ወደውጭ ሀገር በመሄድ ቀደም ሲል በተማሩበት ትምህርት ቤት በመግባት የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አገኙ። በ1973 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በቀድሞው የአካል ማሠልጠኛና ስፖርት ኮሚሽን መሥሪያ ቤት ተመድበው ሲሠሩ ቆዩ።

ከ 1977 ዓ.ም. ጀምሮ በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን በአሠልጣኝነት ተመድበው በ800፣ በ1,500፣ በ10,000 እና እንዲሁም በማራቶን እያሠለጠኑ ብዙ አትሌቶችን ለውጤት አብቅተዋል። ወልደመስቀል ኮስትሬ (ዶ/ር) የዓለም ምርጥ የአትሌቲክስ አሠልጣኝ በመሆን በኅዳር ወር 1999 ዓ.ም. በፈረንሣይ አገር በሞናኮ ከተማ ተሸላሚ ለመሆን ችለዋል። ከሦስት አሥርታት በላይ በአትሌቲክሱ ዓለም ላቅ ያለ ተግባር ማከናወናቸው የተገነዘበው ኢንተርናሽናል አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች ማኅበር «ከኮከብም የሚበልጥ ኮከብ» አለ በማለት ነው ወልደመስቀል (ዶ/ር) ዓለም አቀፍ እውቅና የሰጠው።

ወልደመስቀል (ዶ/ር) በስፖርት ዘርፍ ለሀገር ላበረከቱት የላቀ አስተዋፅዖ የ2007 ዓ.ም. «የበጎ ሰው ሽልማት» በስፖርት ዘርፍ ተቀብለዋል።

ወልደመስቀል ኮስትሬ (ዶ/ር) በአሠልጣኝነት ዘመናቸው ካፈሯቸው ስመጥር አትሌቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡- ኃይሌ ገ/ሥላሴ፤ ሚሊዮን ወልዴ ፤ደራርቱ ቱሉ ፤ፊጣ ባይሳ፤ ጌጤ ዋሚ፤ ቀነኒሳ በቀለ፤ አሰፋ መዝገቡ፤ ስለሺ ስህን፤ ወርቅነሽ ኪዳኔ፤ ጥሩነሽ ዲባባ ፤መሠረት ደፋር እና ሌሎች በርካታ አትሌቶችን አፍርተዋል።

ወልደመስቀል (ዶ/ር) የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድንን ይዘው በተሳተፉባቸው አምስት ኦሎምፒኮች ላይ 28 ሜዳሊያዎችን ለሀገራቸው አስገኝተዋል (13 ወርቅ 5 የብር እና 10 የነሐስ ሜዳሊያን ማምጣት ችለዋል።)

በሮም ኦሊምፒክ የአበበ ቢቂላ ድል (ጳጉሜን 5 ቀን 1952 ዓ.ም.) በኋላ በወንዶች ብቻ የተገደበው የኢትዮጵያውያን የኦሊምፒክ ድል፣ በሴቶች በኩል ፍሬ ማፍራት የጀመረው ግን በ1984 ዓ.ም. ነበር፡፡ በባርሴሎና ኦሊምፒክ በዕንቁዋ ደራርቱ ቱሉ የ10,000 ሜትር ወርቃማ ድል፡፡ አበበ ቢቂላን ለድል እንዳበቁት አሠልጣኙ ሜጀሪ ኦኒ ኒስካነን ሁሉ የሴቶች ፋና ወጊ ድል የተገኘው በወልደመስቀል ኮስትሬ (ዶ/ር) አሠልጣኝነት ነበር፡፡

ከሞስኮ ኦሊምፒክ (ሐምሌ 1972 ዓ.ም.) በማጣሪያ ተፎካካሪነት ብቻ ተገድቦ የነበረው የኢትዮጵያውያት አትሌቶች የሩጫ ጉዞ በወርቅ መታጀብ የጀመረው ባርሴሎና ላይ ነበር፡፡ በአራት ዓመቱ አትላንታ ላይ ቀጠለ፡፡ በታዋቂው አሠልጣኝ ንጉሤ ሮባ ዘመን በሞስኮ ኦሊምፒክ (1972 ዓ.ም.) በ5,000 እና በ10,000 ሜትር ወርቆችን ያገኘው ምሩፅ ይፍጠር የድል ሰንደቅ ዳግም ሕይወት የዘራው ከአራት ኦሊምፒያድ 16 ዓመት ቆይታ በኋላ ነበር፡፡

በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ታሪክ በተለይ ከባርሴሎና ኦሊምፒክ ወዲህ በውጤታማነት ከተገኙባቸው የመጨረሻዎቹ አምስት ኦሊምፒያዶች የተመዘገቡት 28 ሜዳሊያዎች (13 ወርቅ፣ 5 ብርና 10 ነሐስ) ወልደመስቀል (ዶ/ር) የዋና አሠልጣኝነት ትሩፋቶች ናቸው፡፡

ወልደመስቀል (ዶ/ር) ከአሠልጣኝ ንጉሤ ሮባ ኅልፈት በኋላ የኢትዮጵያ አትሌትክስ ብሔራዊ ቡድን የዋና አሠልጣኝነት በትሩን በመቀበል ከባርሴሎና እስከ ቤጂንግ በተካሄዱት ኦሊምፒኮች፣ እንዲሁም በስምንት የዓለም ሻምፒዮናዎች በውጤታማነት የላቀ አበርክቶ ማኖር ችለዋል።

## የስመ ጥር አትሌቶች ምስክርነት፡-

አትሌት መሰለች መልካሙ፡- ከዶክተር ጋር ለረጅም ጊዜ ባልሠራም በቤጂንግ ኦሊምፒክ የመሠልጠን ዕድሉ ነበረኝ። ጥሩና ጠንቃቃ አሠልጣኝ መሆናቸውን እኔ ብቻ ሳልሆን ሁሉም አትሌትና የስፖርት ቤተሰብ የሚያውቀው ነው። እኔም ከዚህ የበለጠ እሳቸውን የምገልጽበት ቃላት የለኝም። በአጠቃላይ ምትክ የሌላቸው ውጤታማ አሠልጣኝ ናቸው።

ወልደመስቀል (ዶ/ር) ከሌሎች አሠልጣኞች ብዙ የሚለዩባቸው ብቃቶች አሏቸው። ሥራ ላይ ቀልድ አያውቁም። ከልባቸው ነው የሚያሠሩት። ደከመኝና ሰለቸኝ የማይሉ ታታሪ አሠልጣኝ ናቸው። በተፈጥሯቸው በጣም ለየት ያሉ ናቸው። ለሥራ ያላቸው ሥነ ምግባር በተለይ በጣም አስገራሚና ሁላችንም ልንወርሰው የሚገባ ነገር ነው።

ስለእሳቸው በጣም የሚቆጨኝ ነገር የልምምድና ሥልጠና አሠራራቸው ወደ ሌሎች ተተኪ አሠልጣኞችና ባለሙያዎች የሚተላለፍበት አጋጣሚ አለመኖሩ ነው። ከእሳቸው ብዙ መማር ይቻላልና" ትላለች።

አትሌት ስለሺ ስህን፡- "ወልደመስቀል (ዶ/ር) ከየትኛውም አሠልጣኝ የተለዩ ናቸው። በአትሌቲክስ አሠልጣኝነታቸው ውጤታማና በግል ባሕሪያቸውም ጠንካራ ሰብዕና ያላቸው ናቸው። በአትሌቲክሱ ስፖርት በቂ እውቀት አላቸው። ሥልጠናውን በደንብ ይችላሉ። በሚገባ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ለማን ምን አይነት ሥልጠና መስጠት እንዳለባቸው ያውቃሉ። እያንዳንዱን አትሌትም ጠንካራና ደካማ ጎኑን ለይተውም ያውቃሉ። ለዚህም ነው በሥራቸው ውጤታማ መሆን የቻሉት።

እሳቸው ከሠልጣኝ አትሌቶች ጋር ያላቸው ግንኙነትም በጣም መልካምና የአባትና ልጅ አይነት ነው። አሠልጣኝ ብቻ ሳይሆን እንደአባትም እየተቆጡና እየመከሩ የሚያሠለጥኑ ናቸው። በሁሉም አትሌት ዘንድ የሚከበሩና የሚወደዱ ናቸው። በሥራቸውም በጣም የሚከበሩና ማንም አትሌት በእሳቸው በሠለጠንኩ ብሎ የሚመኛቸው ናቸው። በሕይወት ዘመናቸው ለሰጡን መልካም ነገር ሁሉ መመስገንና መከበር አለባቸው።" ይላል።

አትሌት ወርቅነሽ ኪዳኔ፡- "በወልደመስቀል ኮስትሬ (ዶ/ር) ሁለት ኦሊምፒክና ሦስት የዓለም ሻምፒዮናዎች ላይ ተሳትፌያለሁ። በዚህ ራሴን እንደ ዕድለኛ እቆጥረዋለሁ። ቀደም ሲል እነ ደራርቱንና ጌጤ ዋሚን በሚያሠለጥኑበት ጊዜ ምናለ እኔም በእሳቸው በሠለጠንኩ ስል እመኝ ነበር። ዕድሉን አግኝቼ በመሠልጠኔ ደስተኛ ነኝ። በእሳቸው መሠልጠኔ ጠንካራ አትሌት እንደሆን አድርጎኛል።

እኔን ጨምሮ ብዙ የኢትዮጵያ አትሌቶች ላገኘነው ውጤት የእሳቸው አስተዋፅዖ በጣም የጎላ ድርሻ አለው። በጣም ውጤታማ የሥልጠና መንገድ የሚከተሉ ጠንካራ አሠልጣኝ ናቸው። እሳቸውን የሚተካ አሠልጣኝ እስከአሁን አላገኘንም። በሕይወት ዘመናቸው ካገናጸፉን ክብርና ደስታ አንጻር የሚገባቸውን ክብርና እውቅና አግኝተዋል ብዬ አላስብም። በዚህም በጣም አዝናለሁ። እሳቸው የኢትዮጵያም ሆነ የአፍሪካ ታላቅ አሠልጣኝ ናቸው» ትላለች።

አትሌት ገዛኸኝ አበራ፡- "በትራክ ሩጫዎች ላይ የመሠልጠን ዕድሉን ባላገኝም በቅርበት የማወቅ ዕድሉ ነበረኝ። ከብሔራዊ ቡድናችን ጋር እሳቸው ካሉ በራስ መተማመንና አሸናፊነት በሁላችንም ልብ ውስጥ ይኖራል። ለአትሌቶች ድል የእሳቸው ጠንካራ ሥራና የአሸናፊነት መንፈስ ትልቅ ሚና አለው።

ስለእሳቸው በጣም የሚቆጨኝ ነገር በሕይወት ሳሉ በስፖርቱ ያላቸው እውቀት የሚተላለፍበት መንገድ አለመፈጠሩ ነው። አንድ መጽሐፍ እንኳ አዘጋጅተው ቢሆን ጥሩ ነበር። ቢሆንም በዘመናቸው ላስገኙት ታላላቅ ድሎች ሁሌም ሊመሰገኑና ሊከበሩ ይገባል» ይላል።

ወልደመስቀል (ዶ/ር) በአንድ ወቅት ያጋጠማቸው የከፋው የመኪና አደጋ በተደጋጋሚ በሀገር ውስጥና በውጭ አገሮች ከፍተኛ ሕክምና ሲከታተሉበት ቆይተዋል፡፡ ይህም ተጓዳኝ ሕመም በመፈጠሩ አደባባይ ከመዋል ገድቧቸው ኖሯል፡፡

ሀገራችን በእስካሁኑ የኦሊምፒክ ተሳትፎዋ ካገኘቻቸው ሜዳሊያዎች ውስጥ 28ቱ የተመዘገቡት በወልደመስቀል ኮስትሬ (ዶ/ር) የአሠልጣኝነት ዘመን መሆኑ፣ ለሀገራችን የአትሌቲክስ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ የነበራቸው አሠልጣኝ ስለመሆናቸው ትልቅ ማሳያ ነው።

በ1939 ዓ.ም ረቡዕ ጥር 21 ቀን፣ ከአባታቸው ከአቶ ኮስትሬ ሰበሬና ከእናታቸው ወ/ሮ እናት ገብርኤል ደስታ፣ የተወለዱት ወልደመስቀል (ዶ/ር) እሑድ ግንቦት 7 ቀን 2008 ዓ.ም. ነበር ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት። በ69 ዓመታቸው ያረፉት ዶ/ር ወልደመስቀል የአንድ ወንድ ልጅ አባት ነበሩ።



The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ዘመን
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# “የኢትዮጵያ ታሪክ ከአትሌቲክስና ኦሊምፒክ ውጤት ጋር የተቆራኘ ነው”

**- የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳሕለወርቅ ዘውዴ**

ዓለማየሁ ግዛው

በፓሪስ 2024 ኦሊምፒክ ለተሳተፈው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ትናንት ማለዳ ወደ ሀገሩ ተመልሷል። ምሽቱንም ፕሬዚዳንት ሳሕለ ወርቅ ዘውዴን ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት ለቡድኑ በብሔራዊ ቤተ-መንግሥት የክብር ሽልማት፣ የማበረታቻ እና የእራት ግብዣ መርሐ-ግብር ተካሂዷል። በመርሐ-ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት ፕሬዚዳንት ሳሕለወርቅ፣ በፓሪስ ኦሊምፒክ የመክፈቻ ሥነሥርዓት ላይ በተገኙበት ወቅት ብዙዎች ኢትዮጵያ በርካታ ሜዳሊያ እንደምታገኝ ሲገልፁላቸው እንደነበረ አስታውሰዋል። ይህም ኢትዮጵያና የኦሊምፒክ አትሌቲክስ ከውጤት ጋር የተቆራኘ መሆኑን ማሳያ አድርገው ጠቅሰዋል። ፓሪስ ላይ በከፍተኛ ተጋድሎ ሜዳሊያ ያስመዘገቡና ውጤት ለማምጣት ለጣሩት ሁሉ ምስጋና አቅርበዋል።

ፕሬዘዳንቷ ባለፈው ቶኪዮ 2020 ኦሊምፒክ ወቅት ቡድኑን ሲቀበሉ ከሦስት ዓመት በፊት ያደረጉትን ንግግር በመድገም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአትሌቶቻችንን ድል አድራጊነትና የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊነት የመጠበቅ ባሕል ቢኖረውም ቶኪዮ ላይ ይህንን ማሳካት እንዳልተቻለ አስታውሰው ያለፈው ንግግራቸው ለአሁኑ የፓሪስ ውጤትም እንደሚሠራ ለማስረዳት ሞክረዋል። ችግሮች ሲፈጠሩ መመርመርና ማወቅ ብሎም ለቀጣይ ማስተካከል እንደሚገባ የተናገሩት ፕሬዚዳንቷ ፓሪስ ላይ የተፈጠሩ ችግሮችን በዝምታ ማለፍ እንደማይገባ ገልፀዋል። በዚህም ለቀጣይ ኦሊምፒክ ችግሮችን ቀርፎ መዘጋጀት የሚገባው ካሁኑ መሆኑን ጠቁመዋል። “የአትሌቲክስና ኦሊምፒክ ተቋማዊ ብቃታቸው ሊፈተሽና ሊታይ ሊመረመር ይገባል፣ የዓለምን ሁኔታ በሚመጥን መልኩ ዳግም ሊዋቀሩ ይገባል” በማለትም በቶኪዮ ኦሊምፒክ መልስ ያደረጉትን ንግግር ደግመው አቅርበዋል።



**ቡድኑ በቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ አቀባበል የተደረገለት ሲሆን በብሔራዊ ቤተመንግሥትም ሽልማት ተበርክቶለታል፣**

የኢትዮጵያ ውጤት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰና ሌሎች ሀገሮች እየበለጡን በመሆኑ ይህን የውጤት ቀውስ መቀረፍ ይኖርበታልም ብለዋል። የሀገር ኩራት የሆኑ አትሌቶቻችን በዓለም አደባባይ ማምጣት የሚችሉትን ውጤት እንዲያመጡ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ መሥራት ያለባቸው የቤት ሥራ እንዳለም ፕሬዚዳንቷ አሳስበዋል።

በሽልማት መርሐግብሩ ውጤት ባይቀናቸውም ለተሳተፉ አትሌቶች ከ75 ሺ ብር እስከ 300 ሺ ብር የማበረታቻ ሽልማት ተበርክቷል። ከፍተኛ ተጋድሎን በማድረግ የብር ሜዳሊያን ያስመዘገቡ አትሌቶች አራት ሚሊዮን ብር ሲሸለሙ ብቸኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ያስመዘገበው አትሌት ታምራት ቶላ የ7 ሚሊዮን ብርና የወርቅ ኒሻን ተሸላሚ መሆን ችሏል። ጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለም ላደረገው ጥሩ ተሳትፎ ከፍተኛ የወርቅ ኒሻን ተሸላሚ ሆኗል። ለአሠልጣኞች ከ50 ሺ ብር ጀምሮ አትሌቶቻቸው እንዳስመዘገቡት ውጤት የተለያየ መጠን ያለው የገንዘብ ሽልማት ተበርክቷል። የወርቅ ላመጣ አሠልጣኝ የ 2 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ሽልማት ተበርክቷል። አትሌት ለሜቻ ግርማ በልዩ ተሸላሚነት 2 ሚሊዮን ብር ተሸልሟል።

የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ፣ የኦሊምፒክ ስፖርት ሀገራት በአንድ መንደር ተሰባስበው የሀገራቸውን ገጽታ የሚገነቡበትና ሰንደቅ ዓላማቸውን ከፍ የሚያደርጉበት ሠላማዊ መድረክ እንደሆነ ተናግረዋል። ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን በታሪካዊ ድሎችም ጭምር በዓለም ዘንድ ትጠበቃለች። ይህም የሆነው በትብብር የማይቻለውን ሁሉ ችለን ስለምናሳይ ነውም ብለዋል። የተመዘገበው ውጤት አበረታች ቢሆንም የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ተሳትፎ ውጤታማነት ከጊዜ ወደ ጊዜ ብርቱ ፈተና እንደገጠመው ያለፉት ሁለት ኦሊምፒኮች ማሳያ እንደሆኑም ገልጸዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ለሚታዩ ችግሮች ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት በጥናትና ውይይት ከአሠራር፣ አደረጃጀትና አመራር አንጻር የሚታዩ ማነቆዎችን ለመፍታት በልዩ ትኩረት ይሠራል ብለዋል።